በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት

የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት አሰጣጥ

ማስልጠኛ ሰነድ

ሰኔ 2017 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ይህ የማሰልጠኛ ሰነድ በኢትዮጵያ ኢንርፕራይዝ ልማት አስተባባሪነት፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ የፋይናንስ ድጋፍ ከካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተቋማት እና ከኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት በተውጣጡ ከፍተኛ ልምድ ባላቸው አመራሮችና ባለሙያዎች የተዘጋጀ ነው፡፡

	አዘጋጅ		
ተ.ቁ	ስም	ሚና	ተቋም
1	አቶ ሲራክ ማሞ ኃይለመለኮት	አስተባባሪ	ኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት
2	አቶ አሰፋ ካሕሳይ	አባል	አዲስ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ሥራ አ/ማ
3	አቶ አብዲሳ ዳቤሳ	አባል	ኦሮሚያ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ሥራ አ/ማ
4	አቶ ደረጀ አስራት	አባል	ኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት

ማውጫ

መግቢያ 3

ክፍል አንድ 8

1. ትርጓሜ 8

2. የሰነዱ አስፈላጊነት እና ስልጠናው የሚሠጥበት ስልት 10

2.1. የሰነዱ አስፈላጊነት 10

2.2. ስልጠናው የሚሠጥበት ስልት 11

3. ዋና ዓላማ 12

3.1. ዝርዝር ዓላማዎች 12

4. የማሰልጠኛ ማኑዋሉ የተፈፃሚነት ወሰን 12

5. መርሆዎች 12

ክፍል ሁለት 13

2. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማትና የሚሰጧቸው አገልግሎቶች 14

2.1. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ለማግኘት የሚደረጉ የቅድመ-ዝግጅት ሥራዎች፤ 15

2.2. የግንዛቤ ፈጠራና የማስተዋወቅ ሥራዎች 15

2.3. የካፒታል ዕቃ ተጠቃሚዎች የፍላጎት ጥናትና ልየታ 16

ክፍል ሶስት 17

3 የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት አሰራር ሥርዓት 17

3.1. የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ዓይነቶች 18

3.1.1 የዱቤ ግዢ / Hire Purchase/ 18

3.1.2 የፋይናንስ ኪራይ /Financial Lease/ 18

3.1.3 የምክር አገልግሎት 19

3.2. አገልግሎት ለማግኘት የሚሟሉ ቅድመ-ሁኔታዎችና የሥራ መስኮች 19

3.3 የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት 21

3.4 የካፒታል ዕቃ ዓይነትና የማሽን አምራች ወይም አቅራቢዎችን ስለመለየት 21

3.5 የካፒታል ዕቃ ኪራይ ውል ስምምነት ስለማድረግ፤ 22

3.6 የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኪራይ ክፍያ እና የሊዝ ዘመን አወሳሰን ሥርዓት 23

3.7. የካፒታል ዕቃ ማጓጓዝና ርክክብ ስለማከናወን 25

3.8. የካፒታል ዕቃዎች ኢንሹራንስ መግባት፣ 26

3.9 የካፒታል ዕቃ ተከላ፣ ሙከራ እና የአጠቃቀም ሥልጠና 26

3.10. የካፒታል ዕቃ ምዝገባ እና የውል ምዝገባ ስለማከናወንና 26

3.11. የካፒታል ዕቃ አያያዝ፣ ጥገናና ዕድሳት ስለማድረግ 27

3.12. የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ስለማከናወን 28

3.13. የአከራይ እና ተከራይ ውል የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎችና ቀጣይ የሚወሰዱ እርምጃዎች 28

3.14. የካፒታል ዕቃ አቅራቢና የአከራይ ውል የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎችና ቀጣይ የሚወሰዱ እርምጃዎች 29

ክፍል አራት 30

4. የፈጻሚ አስፈጻሚ እና የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት 30

4.1. ፈጻሚ አካላት 30

4.2 አስፈጻሚ አካላት 36

4.3 ባለድርሻ አካላት 37

5. በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ከባለድርሻ ተቋማት ጋር ተያይዞ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች 35

6. የማጣቀሻ ጽሁፎች 41

7. አባሪዎች 42

መግቢያ

ሀገራችን በ2022 ዓ.ም መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ በምታደርገው ርብርብ ወሳኝ እና ዋነኛ ከሆኑት ጉዳዮች ውስጥ የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ልማትን በማፋጠን ኢኮኖሚያችን ወደ ኢንዱስትሪ መዋቅራዊ ሽግግር እንዲያድግ ማስቻል ነው፡፡

ለዚህም የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ልማቱ ያሉበትን ማነቆዎች በጥናት ለይቶና ያንን ሊፈቱ የሚችሉ አሰራሮችን ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረጉ መሄድን ይጠይቃል፡፡ አነስተኛና መካከለኛ የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ካሉባቸው ተግዳሮቶች መካከል አንዱ የማምረቻ መሳሪያዎች/ቴክኖሎጂዎች ዘመናዊ አለመሆናቸው ሲሆን ይህም በምርታማነታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በማሳረፍ በዋጋ ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ ከማድረጉም በላይ ከሚጠቀሙባቸው ኋላቀር ማምረቻ መሳሪያዎች ጋር ተያይዞ በምርት ጥራትና በአቅርቦት ጊዜ ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ ማድረጉም የማይቀር ነው፡፡

እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ራስን በዘመናዊ ማምረቻ መሳሪያዎች ማደራጀት የሚጠይቅ ቢሆንም ለዚሁ የሚያስፈልጋቸው ገንዘብ ከፍ ያለ ከመሆኑም ባሻገር ይህንን ገንዘብ በብድር ለማሟላት የሚጠየቁትን ዋስትናም ለማቅረብ አይችሉም፡፡ በመሆኑም ከማምረቻ መሳሪያ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ችግሮችን በራሳቸው አቅም መሻገር የሚችሉት ኢንተርፕራይዞች በቁጥር ውስን የሆኑና የተሻለ የፋይናንስ አቅም ወይም ለዚህ የሚሆን በቂ ዋስትና ያላቸው መሆናቸው አይቀርም፡፡

በመሆኑም መንግስት በማፋክቸሪንግ ዘርፉ የተሰማሩ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የማምረቻ መሳሪያ በካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት አሰራር ያለ ዋስትና (የሚቀርበውን ማምረቻ መሳሪያ ራሱ ማሽነሪውን ዋስትና በማድረግ) የሚያገኙበት አሰራር ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ለዚህም በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥቶ የነበረውን የካፒታል ዕቃ ንግድ ስራ አዋጅ ቁጥር 103/1990 በአዋጅ ቁጥር 807/2005 በማሻሻል ተግባራዊ እንዲሆን አድርጓል፡፡ ይህ አሰራር ተግባራዊ በሚደረግበት ጊዜ ዘርፉን ለማበረታታት መንግስት ለተጠቃሚዎች ከሚሰጣቸው ድጋፎች/ማበረታቻዎች መካከል ለማምረቻ መሳሪያ ግዢ በአንድ ጊዜ ከፍተኛ ገንዘብ ሳያወጡ ክፍያውን በረዥም ጊዜ በሚፈጸም የዱቤ ግዥ ስርዓት ማሽነሪ ባለቤት የሚሆኑበት፤ ለሚሰጠው የካፒታል ዕቃ ኪራይ ተጨማሪ ዋስትና ማቅረብ የማይጠበቅባቸው መሆኑ፣ ለዚህ አገልግሎት ከውጭ የሚገቡ የካፒታል ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ መሆናቸውና እና ከአገር ውስጥ የሚቀርቡ የካፒታል እቃዎችም ከተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ነጻ መሆናቸው የሚሉት ይገኙባቸዋል፡፡

ይህን አገልግሎት እንዲሰጡ በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ አግኝተው የተቋቋሙ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ስራ አክሲዮን ማህበራት እና ይህን አገልግሎት እንዲያቀርብ ተጨማሪ ተልዕኮ የተሠጠው የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ባሏቸው ቅርንጫፎች በኢንተርፕራይዞቹ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ድጋፍ በማቅረብ ላይ ይገኛሉ፡፡

በመሆኑም የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ማነቆ የሆነውን የማምረቻ መሳሪያዎች ችግር በመፍታትና የማምረት ዘርፉን ልማት በማፋጠን በአገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገቱ ውስጥ ዘርፉ የሚኖረውን ድርሻ ለማሳደግ የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ስርዓቱን ምንነት፣ በዚህ አሰራር ተጠቃሚ ለመሆን መሟላት ስላለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎችና በሂደቱ የሚኖረውን የአስፈጻሚና የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት ለማመላከት የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት በደንብ ቁጥር 526/2015 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት አሰጣጥ ማስልጠኛ ሰነድ አዘጋጅቷል፡፡

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ተልዕኮ፣ ራዕይና ዕሴቶች

ተልዕኮ

የዘርፉን ልማት ለማፋጠን የሚረዱ የድጋፍ ማዕቀፎች በማዘጋጀትና በመተግበር፤ የባለድርሻ አካላትንና የአምራች ኢንተርፕራይዞችን አቅም በመገንባት፤ ሁሉን አቀፍና ውጤታማ ድጋፎችን በመስጠት፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ እንዲስፋፋና እንዲጠናከር በማድረግ ገቢ ምርቶችን መተካት፤ የኤክስፖርት አቅምን ማሳደግ፤ የስራ እድልን ማስፋትና በአገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ የዘርፉን ድርሻ ማሳደግ፤ የዜጎችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፡፡

ራዕይ

በ2022 በአፍሪካ የተወዳዳሪነት ተምሳሌት የሆነና በአገራችን ኢኮኖሚ የላቀ ድርሻ ያለው የአነስተኛና መካከለኛ አምራች ዘርፍ ተገንብቶ ማየት!

ዕሴቶች

- ታታሪ፣ ብቁና ተወዳዳሪ የሰው ሃብት ማፍራት፤
- ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈን፤
- ለቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት መትጋት፤
- የተሳለጠ ቅንጅታዊ አሰራር ማስፈን፤
- አዳዲስ አሠራርና ፈጠራን ማበረታታት፤
- እድገት፣ ጥራትና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ማበረታታት፤
- አሳታፊነት፣ ፍትሃዊነትና ተደራሽነትን ማረጋገጥ፤
- በአገር ምርት መኩራት፤
- ተአማኒ፤ ተደራሽና ወቅታዊ የመረጃ ስርአት መዘርጋት፤
- ለማያቋርጥ ለውጥ ዝግጁ መሆን፤

ክፍል አንድ

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተቋማት አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ለአገራችን ኢንዱስትሪ ዕድገት የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑ በመረዳት በካፒታል ዕቃዎች አቅርቦት የሚያጋጥሟቸው ተግዳሮቶች ለመቅረፍ በአዋጅ የተቋቋሙ ድርጅቶች ናቸው፡፡ በዚሁ መሰረት በስልጠና ግንዛቤአቸውን በማሳደግ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል ሰነዱ ሲዘጋጅ አስፈላጊነቱ፣ ዓላማውና መርሆዎቹ በዚህ ክፍል ተቀምጠዋል፡፡

1. ትርጓሜ

1.1 **"ማከራየት"** ማለት አከራይ አንድን የካፒታል ዕቃ በፋይናንስ ኪራይ ወይም በዱቤ ግዥ ስምምነት መሰረት ያለምንም መያዣ/ኮላተራል/ በየተወሰነው ክፍለ-ጊዜ የሚፈፀም ክፍያ እየተቀበለ በኪራይ ለተወሰነ ጊዜ ለምርትና ለአገልግሎት መስጠት ዓላማ እዲጠቀምበት በዓይነት የሚደረግ የካፒታል ፋይናንስ አቅርቦት ነው፡፡

1.2 **"አከራይ"** ማለት የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ሥራ አክስዮን ማህበራት እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ማለት ነው፡፡

1.3 **"ተከራይ"** ማለት በኪራይ ስምምነት መሰረት ለተወሰነ ጊዜ አንድን የካፒታል ዕቃን ኪራይ ከፍሎ ለመጠቀም ከአንድ አከራይ ላይ የተዋዋለ ግለሰብ ወይም ማህበር ነው፡፡

1.4 **"የኪራይ ክፍያ"** ማለት ተከራዩ ከአከራዩ ለተከራየው ዕቃ በተስማሙበት የኪራይ ዋጋና የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የሚከፈል የገንዘብ መጠን ነው፡፡

1.5. **"የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ"** ማለት የፋይናንስ ኪራይና የዱቤ ግዥን ያጠቃልላል፡፡

1.6. **"የዱቤ ግዥ"** (Hire purchase) አከራይና ተከራይ ባደረጉት ስምምነት መሰረት አከራይ በተወሰነ ጊዜ የሚደረግ ክፍያ እየተከፈለው አንድ የተወሰነ የካፒታል ዕቃ ተከራዩ እንዲጠቀምበት የሚፈቅድበት፣ እያንዳንዱ የኪራይ ክፍያ በተደረገ ቁጥር ለክፍያው ተመጣጣኝ በሆነ መቶኛ ልክ ለተከራዩ የባለቤትነት መብት የሚተላለፍበትና ተከራዩ የመጨረሻውን ክፍያ እንደፈጸመም በካፒታል ዕቃው ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት ወዲያውኑ የሚያገኝበት የኪራይ ዓይነት ነው፡፡

1.7. **"የፋይናንስ ኪራይ"** /Financial lease/ ማለት አከራዩ ቀደም ሲል ይዞት የሚገኘውን የካፒታል ዕቃ፤ ወይም በተከራዩ መራጭነት አቅራቢ ተብሎ ከሚጠራው ሦስተኛ ወገን የሚገዛውን የካፒታል ዕቃ ተከራዩ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ተከፍሎ የሚያልቅ በሁለት

ወገኖች ስምምነት የተወሰነ ክፍያ በተወሰነ ጊዜ በመፈጸም እንዲጠቀምበት የሚያከራይበት፣ የኪራይ ስምምነት ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ አከራዩ በካፒታል ዕቃው ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት ይዞ የሚቆይበትና የኪራይ ዘመኑ ሲያበቃ ሁለቱም ወገኖች ከተስማሙ ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን ሊገዛ የሚችልበት ካልተስማሙ ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን ለአከራዩ የሚመልስበት የኪራይ ዓይነት ነው፡፡

1.8. **"የካፒታል ዕቃ"** ማለት ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ማንኛውም መሳሪያ ወይም ማሽን ሲሆን አክሰሰሪዎችን ይጨምራል፤

1.9. **"አቅራቢ"** ማለት ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት የሚውሉ መሳሪያዎችን በሀገር ውስጥ አምርተው ወይም ከውጭ ሀገር አስገብተው የሚሸጡ ተቋማት ናቸው፡፡

1.10. **"መልሶ መውሰድ"** ማለት የካፒታል ዕቃ ተከራዩ ግዴታውን በአግባቡ ሳይወጣ ሲቀር አከራዩ የካፒታል ዕቃውን መልሶ መረከብ ማለት ነው፡፡

1.11. **"ሊሠረዝ የማይችል ስምምነት"፡-** ማለት በሕግ አፈጻጸም ወይም በስምምነት ብቻ ካልሆነ በስተቀር ሊሠረዝ የማይችል የኪራይ ስምምነት ነው፡፡

1.12. **"የእፎይታ ጊዜ"** ማለት አንድ ተከራይ የዋና ዕዳውን ክፍያ የማይጀምርበት ጊዜ ነው፡፡

1.13. **"ኢንሹራንስ"፡-** ማለት አንድ የካፒታል ዕቃ የእሳት እና የዝርፊያ/Fire and burglary Insurance/ ወይም ማሽነሪው ሊኖረው ከሚችል የአደጋ ስጋት አንጻር የሚደረግ የተለያየ የኢንሹራስ ሽፋን አደጋ ቢደርስበት ለጉዳቱ ካሳ የሚከፈልበት የመድን ሥርዓት ነው፡፡

1.14. **"መዝጋቢ አካል"** ማለት ንግድ ሚኒስቴር ወይም የካፒታል ዕቃዎችን እና የካፒታል ዕቃ ኪራይ ስምምነቶችን የመመዝገብ ሥልጣን የተሰጠው የክልል/የከተማ አስተዳደር አካል ነው፡፡

1.15. **"የካፒታል ዕቃ የዋስትና ምዝገባ"** ማለት ለተከራይ የተላለፈ የካፒታል ዕቃ መረጃ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተንቀሳቃሽ ንብረት ዋስትና ምዝገባ ጽ/ቤት የሚመዘገብበት አሰራር ነው፡፡

1.16. **"የማምረቻና የመሸጫ ማዕከላት"** ማለት በየከተማው በምርት ስራዎች ላይ ለተሰማሩና በተወሰነ አካባቢ ተሰባስበው አንድ ዓይነት ወይም ተመጋጋቢ ምርቶችን በማምረት

በጋራ ተጠቃሚ ለመሆን የሚሹ ኢንተርፕራይዞችን ለማስተሳሰርና ለመደገፍ የተደራጁ ማምረቻ በታዎች ናቸው፡፡

1.17. **"አምራች"** ማለት ማሽንን፣ መሳሪያን ወይም ጉልበትንና እውቀትን በመጠቀም በጥሬ ዕቃ ላይ የቅርጽ፣ ወይም የይዘት ለውጥ በማድረግ የተሻለ ዋጋ ያለው ምርት የሚያመርት ነው፡፡

1.18. **"አነስተኛ አምራች ኢንተርፕራይዝ"** ማለት ከ 11 እስከ 50 ቋሚ ሰራተኞች የያዘ እና ከብር 600,001 እስከ ብር 10 ሚሊዮን ጠቅላላ ሐብት ያለው ኢንተርፕራይዝ ነው፤ ሆኖም ግን በሰው ኃይልና በጠቅላላ ሐብት መካከል አሻሚ ሁኔታ ሲፈጠር ጠቅላላ ሐብት ገዥ መስፈርት ይሆናል፤

1.19. **"መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዝ"** ማለት ከ 51 እስከ 100 ቋሚ ሰራተኞች የያዘ እና ከብር 10,000,001 እስከ 90 ሚሊዮን ጠቅላላ ሐብት ያለው ኢንተርፕራይዝ ነው፤ ሆኖም ግን በሰው ኃይልና በጠቅላላ ሐብት መካከል አሻሚ ሁኔታ ሲፈጠር ጠቅላላ ሐብት ገዥ መስፈርት ይሆናል፤

1.20. **"ሚኒስቴር"** ማለት የኢንዱስትሪ ሚንስቴር ነው፡፡

1.21. **"ደንብ"** ማለት የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማትን አደረጃት፣ ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው ደንብ ቁጥር 526/2015 ማለት ነው፡፡

2. የሰነዱ አስፈላጊነት እና ስልጠናው የሚሠጥበት ስልት

የዚህ ሰነድ ዋናው አስፈላጊነት የሚመለከታቸው ተቋማት ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች የተቋማቱን መመሪያዎች እና አሰራሮች የጋራ በማድረግ ሰነዱ ለስልጠና ማዘጋጀት ነው፡፡ በስልጠናውም ወቅት ኢንተርፕራይዞቹ የቡድን ውይይት፣ የልምድ ልውውጥ፣ የመስክ ጉብኝት፣ የምርጥ ተሞክሮ ልውውጥ፣ መልመጃዎችን በመስጠት፣ ወ.ዘተ.. የስልጠና አስጣጥ ሂደት በማጠናከር የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ለማስቻል ነው፡፡

2.1. የሰነዱ አስፈላጊነት

2.1.1. አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ስለ ካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎቱ በቂ ግንዛቤ የሌላቸው መሆኑና ይህን በማሻሻል ዘርፉን የድጋፉ ተደራሽ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ፣

2.1.2. በዘመናዊ የማምረቻ ማሽኖች የማይጠቀሙ በማምረት ስራ ላይ የተሰማሩ እና የሚሰማሩ በርካታ ኢንተርፕራይዞች እንዳሉ ስለሚታወቅ በገበያ ተወዳዳሪ ለመሆን እንዲያስችላቸው የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረጉ አስፈላጊ በመሆኑ፤

2.1.3. የማሰልጠኛ ሰነዱ በሊዝ ክፍያ አሰባሰብ ፈጻሚና ባለድርሻ አካላት የተቀናጀ ተሳትፎ ስለሚኖር ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተቋማት እገዛ የሚያደርግ መሆኑ፤

2.1.4. የፋይናንስ ተቋማት ትኩረት ሊያደርጉባቸው የሚገባ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራዞች ቢሆኑም በዚህ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ የዕቃ ኪራይ አገልግሎት ፋይናንስ ተጠቃሚዎች ቁጥር አነስተኛ በመሆናቸው በስፋት ለማጠናከር የሚጠቅም በመሆኑ፤

2.2. ስልጠናው የሚሠጥበት ስልት

በዚህ የማሰልጠኛ ሰነድ ላይ ለአዳዲስ የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት መካከለኛ አመራሮችና ባለሙያዎች እንዲሁም ለክልል እና ከተማ አስተዳደሮች አመራሮችና ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት እና የዞን፣ የከተሞችና የወረዳዎችን የዘርፉ ልማት መዋቅር አመራርና ባለሙያዎችን ስልጠና እንዲሠጡ በመከታተል እና በመደገፍ፤ በታችኛው የዘርፉ የአደረጃጀት እርከን ላይ የሚገኙና ስልጠና የወሰዱ አመራሮችና ባለሙያዎች ለኢንተርፕራይዞች ስልጠና እንዲሰጡ በማድረግ ይፈጸማል፡፡

ስልጠናውን የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ከካፒታል ዕቃ አቅራቢ የፋይናንስ ተቋማት እና ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ጋር በመቀናጀት በዚሁ የስልጠና ሰነድ ያልተካተቱ መረጃዎችም ካሉ በመጨመር፣ የተለያዩና አስፈላጊ መመሪያዎች፣ አሰራሮች እና ሰነዶች በገለጻ በማቅረብ፣ በቡድን ውይይት፣ በፋይናንስ ተቋማቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በአካል በመገኘትና በመጎብኘት፣ የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞችን ተሞክሮ በማሳየት፣ እንዲሁም በሶሺያል ሚድያዎችና በብሮሸሮች በተለያዩ መንገዶች የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

ከሥልጠናው የሚጠበቁ ውጤቶች

- የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች እንዲሁም የዘርፉ መዋቅር አመራርና ባለሙያዎች በሊዝ ፋይናንስ አሰራር ላይ ያላቸውን ግንዛቤና ዕውቀት ማሳደግና ስራቸውን

ለማሳካት እና ችግር ለመፍታት አዳዲስ ስልቶችን እንዲጠቀሙ ማስቻልና የሚታይ የባህሪ ለውጥ ማምጣት፤

- የማምረቻ መሳሪያ አቅርቦት በማመቻቸት ኢንተርፕራይዞችን ተጠቃሚ ለማድረግ የተያዙ ግቦችን በማሳካት ለዘርፉ ምርታማነትና ተወዳዳሪነት አወንታዊ ሚና መጫወት፤

3. ዋና ዓላማ

አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በቂ ግንዛቤ በማግኘት የሚፈልጓቸውን የማምረቻ መሳሪያዎች በካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት አሰራር ስርዓቱ የተቀላጠፈ አገልግሎት በማግኘት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ነው፡፡

3.1. ዝርዝር ዓላማዎች

- ➢ አነስተኛና መካከለኛ የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ስለ ካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎቶች በቂ የሆነ ግንዛቤ እንዲያኙ ለማድረግ
- ➢ ኢንተርፕራይዞቹ ዘመናዊ የካፒታል ዕቃዎች ተጠቃሚ ለመሆን ካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ተቋማት የተቀላጠፈ አገልግሎት ለማግኘት በየደረጃው በሚገኙ የሚመለከታቸው አካላት ስለሚሰጡት የድጋፍ ዓይነቶች ግንዛቤ ለማግኘት
- ➢ አነስተኛና መካከለኛ ማፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ምርታማነታቸውን ለማሳደግ አስፈላጊ የሆኑ የማምረቻ ማሽነሪዎች ለይተው እንዲቀርቡ ለማድረግ፤

4. የማሰልጠኛ ማኑዋሉ የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ሰነድ በአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ልማት ዘርፍ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ እና በዚህ ዘርፍ ለመሰማራት ሌሎች ቅድመ-ሁኔታዎችን ያሟሉ ተገልጋዮችን የማምረቻ መሳሪያ ጥያቄ በተዘረጋው የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት አሰራር ስርዓት እንዲቀርብላቸው ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ላይ ይወሰናል፡፡

5. መርሆዎች

5.1. የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት በዋናነት ትኩረት በተሰጣቸውና በተመረጡ የማምረት ስራ መስኮች በአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ደረጃ ለተሰማሩና መሰማራት ለሚፈልጉ ተገልጋዮች ትኩረት ይሰጣል፡፡

5.2. የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት አሠራር ኢንተርፕራይዞቹ ያለባቸውን የፋይናንስ ጫና በሚቀንስ መልኩ ይተገበራል፡፡

5.3. የካፒታል ዕቃ ግዥ ሥርዓቱ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን ፍላጎት ያረጋገጠ ይሆናል፡፡

5.4. በካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ኢንተርፕራይዞች ተገቢውን ግዴታ ከተወጡ በኋላ ሙሉ በሙሉ የካፒታል ዕቃውን ባለቤት የሚሆኑበት አሰራር እውን ይሆናል፡፡

5.5. የተከራዮችና የአከራዩ የጥራት መመዘኛ እስከተሟላ ድረስ ማሽነሪዎች ሲገዙ ወይም ጨረታ ሲወጣ ቅድሚያ ለሀገር ውስጥ አምራቾችና አቅራቢዎች ይሆናል፡፡

5.6. የካፒታል ዕቃ አቅራቢ ተቋሙ በሶስትዮሽ ውል የገበያ ትስስር መሠረት የካፒታል ዕቃ የሚያቀርብበት አሰራር ይፈጠራል፡፡

5.7. በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ መሰማራት ለሚፈልጉ ኢንተርፕርነሮች፤ ሴቶች፣ የዩኒቨርሲቲ ምሩቃንና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡

5.8. በአገራችን የተቀረጹ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ መመሪያዎችንና ህጎችን በማክበር ይሰራል፡፡

ክፍል ሁለት

እንደ አገር የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት አመጣጥ ሲታይ በዋናነት ከህንድ፣ ከስሪላንካ እና ከሞሪሽየስ ልምድ በመውሰድ ነው፡፡ የተጠቀሱት አገሮች መንግስታት የካፒታል ዕቃ የፋይናንስ አገልግሎቱን ለማሳለጥ የተለያዩ አዋጆችና ህጎች አውጥተዋል፣ በካፒታል ዕቃ አቅርቦቱም የተለያዩ አቅጣጫዎች በማስቀመጥ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች

ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የፋይናንስ ሊዝ አሰራር ከጊዜ ወደ ጊዜ ዕድገት እያሳየ እንደመጣ ለማየት ተችሏል፡፡

በተለይም ከህንድ አገር በተሞክሮ የታየው የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት እንቅስቃሴ ውጤታማ መሆኑ ነው፡፡ ይህ ተሞክሮ በአገራችን ለተመሰረቱት የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኩባንያዎች ወደ ትግበራ እንዲገቡ ጉልህ ድርሻ ነበረው፡፡ በዚሁ መሠረት የአገራችን አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በካፒታል ሊዝ ፋይናንስ አገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሚመለከታቸው አካላት የተለያዩ እርምጃዎች ሲወሰዱ ቆይተዋል፡፡ በዚህ ክፍል በአገራችን በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኪራይ አዋጅ መሰረት በተቋቋሙት ተቋማት የሚሰጡ ዋና ዋና አገልግሎቶች ተዘርዝረዋል፡፡

2. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማትና የሚሰጧቸው አገልግሎቶች

ወደፊት በአዋጁ መሠረት ሊቋቋሙ የሚችሉ ተቋማት ሊኖሩ የሚችሉ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የስራ ፈቃድ አግኝተው በካፒታል ዕቃ አቅርቦት የተሰማሩትና ስራ ላይ ያሉት ድርጅቶች ከታች የተዘረዘሩ ሲሆን የሚሰጧቸው ዋና ዋና አገልግሎቶችም ተዘርዝረዋል።

ሀ). ኦሮሚያ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ሥራ አ/ማ

ለ) አዲስ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ሥራ አ/ማ

ሐ) ዋልያ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ሥራ አ/ማ

መ) ደቡብ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ሥራ አ/ማ

ሠ) ካዛ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ሥራ አ/ማ

ረ) የኢትዮጵያ ልማት ባንክ

እነዚህ ተቋማት በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥቶ የነበረውን የካፒታል ዕቃ ንግድ ስራ አዋጅ ቁጥር 103/1990 በአዋጅ ቁጥር 807/2005 በተሻሻለው መሠረት የተቋቋሙ መንግስታዊ የልማት ተቋማት ናቸው። የመጀመሪያዎቹ 5 የሊዝ ኩባንያዎች የተመሰረቱት በ2006 ዓ/ም ሲሆን የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ስራው የተመሰረተው በ2009 ዓ/ም ነው።

የሊዝ ኢንደስትሪው በአገራችን አዲስ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በመጀመሪያ ጥቂት ዓመታት ለአገልግሎት ሰጪዎቹም ሆነ ለተገልጋዮች በርካታ ተግዳሮቶች የነበሩ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ

የተቋማቱ ልምድ እየተሻሻለ በመምጣቱ እንዲሁም የተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች ግንዛቤ እየሰፋ በመምጣቱ ችግሮቹ እየቀነሱ መምጣታቸው ይታያል፡፡

በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ድጋፍ አቅርቦት ላይ ተሰማርተው የሚገኙት አምስቱ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ስራ አክሲዮን ማህበራት እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ አባል የሆኑበት የኢትዮጵያ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተቋማት ዘርፍ ማህበር ከ2014 ዓ/ም ጀምሮ ተቋቁሞ ወደ ስራ ገብቷል፡፡ ማህበሩ በሃገራችን ውስጥ በሚገኙ የካፒታል ዕቃ ፋናንስ ተቋማት መካከል የተቀናጀና የተናበበ አገልግሎት እንዲኖር ከሀገር ውስጥ አምራቾችና ከሌሎች የማሽነሪ አቅራቢዎች ጋር በመስራት አገልግሎቱን ፈጣንና ተደራሽ ከማድረግ አንጻር ያሉ ተግዳሮቶችን በጥናት በመለየት ምቹ ሁኔታ በመፍጠርም የጎላ ሚና ይኖረዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አገልግሎቱን የሚሠጡ ተቋማት ባልተቋቋሙባቸው ክልሎች እንዲያቋቁሙ ግንዛቤ በመፍጠርና የቴክኒክ ድጋፍ በማድረግ እየሠራ ይገኛል፡፡

2.1. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ለማግኘት የሚደረጉ የቅድመ-ዝግጅት ሥራዎች፤

አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የካፒታል ፋይናንሱን አገልግሎት ለማግኘት የሚከተሉት ቅድመ ዝግጅቶች ተቀምጠዋል፤

2.2. የግንዛቤ ፈጠራና የማስተዋወቅ ሥራዎች

የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት በሀገራችን በተግባር ላይ ያለ አገልግሎት እንደመሆኑ አገልግሎቱ የኢንተርፕራይዞችን የፋይናንስ ችግር በመፍታት ለምርትና ምርታማነት እና ተወዳዳሪነት ማደግ ብሎም ለአገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት ሊጫወት የሚችለውን ሚና በውል ለማስገንዘብ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በመፍጠር በስፋትና በተደጋጋሚ መስራት ይጠይቃል፡፡

ካሉት አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ምን ያህሉ በገበያ ተወዳዳሪ መሆን በሚያስችሏቸው ዘመናዊ ማምረቻ መሳሪያዎች የተደራጁ ናቸው ብለን ብንጠይቅ እጅግ በጣም ውስን የሆኑት ብቻ እንደሚሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ይህ ሊሆን የቻለበት ዋነኛ ምክንያት ኢንተርፕራይዞቹ ራሳቸውን በአገራዊም ሆነ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ መሆን በሚያስችላቸው ደረጃ ማደራጀት ካለመፈለግ የመነጨ ሊሆን አይችልም፡፡ ይልቁንም ማምረቻ መሳሪያዎቹን ለመግዛት የሚጠይቃቸው የገንዘብ መጠን ከፍ ያለ መሆኑና ይህንን በራሳቸው አቅም

ማሟላት ካለመቻላቸው የተነሳ እንደሚሆን ግልጽ ነው፡፡ ማምረቻ መሳሪያውን ለመግዛት ከሚያስፈልጋቸው ገንዘብ ውስጥ በራሳቸው ቆጥበው ካጠራቀሙት ገንዘብ በላይ ያለውን ልዩነት ከፋይናንስ ተቋማት በመበደር ማሟላት አንዱ አማራጭ ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞቻችን በፋይናንስ አቅማቸው የጎለበቱ አለመሆኑን ተከትሎ የማምረቻ መሳሪያ ለመግዛት የሚያስፈልጋቸውን ገንዘብ አበዳሪ ተቋማቱ የሚጠይቁትን የብድር ዋስትና አቅርበው ብድር ለማግኘት አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል፡፡

በመሆኑም መንግስት የዘረጋው የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት አሰራር የኢንተርፕራይዞችን የካፒታል ፋይናንስ ማነቆ በምን መልኩ እንደሚፈታና ይህንን ድጋፍ ለማግኘት ማሟላት ስላለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች እንዲሁም አገልግሎቱን ከየትኞቹ ተቋማት ማግኘት እንደሚችሉ በዝርዝር ማንሳትና መግባባት መፍጠር ይጠይቃል፡፡

ይህን የግንዛቤ መፍጠር ስራ በመሰረታዊነት ባሉን አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እና ወደ ዘርፉ አዲስ መቀላቀል በሚፈልጉ ኢንተርፕርነሮች ላይ ትኩረት በማድረግ የሚሰራ ቢሆንም ይህንን ስራ በሚገባ መወጣት የሚቻለው የዘርፉን መዋቅር አስቀድመን ተገቢውን ግንዛቤ እንዲጨበጥ ሲቻል ብቻ ይሆናል፡፡

2.3. የካፒታል ዕቃ ተጠቃሚዎች የፍላጎት ጥናትና ልየታ

ከግንዛቤ ማስጨበጫ በኋላ የካፒታል ዕቃ ፍላጎት ያላቸው በማምረት የስራ መስክ ሊሰማሩ የሚፈልጉ አዲስ እና ነባር ኢንተርፕራይዞች የልየታና የፍላጎት ጥናት ይከናወናል፡፡

2.3.1. የካፒታል ዕቃ ተጠቃሚዎች የፍላጎት ጥናት

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት መሠረት የሚያደርገው የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን የካፒታል ዕቃ ፍላጎት በመሆኑ ተጠቃሚ ለሚሆኑ ኢንተርፕራይዞች የሚቀርበው የካፒታል ዕቃ ሊሰማሩ ባሰቡበት ወይም በተሰማሩበት የሥራ መስክ እንዲቀርብላቸው የሚፈልጉትን የማምረቻ መሳሪያ ዝርዝር መግለጫ (Specification) ባካተተ መልኩ መሆኑን በመገንዘብ አቅርቦቱም የኢንተርፕራይዞቹ ፍላጎት መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡ የኢንተርፕራይዞቹ /ኢንተርፕርነሮቹ ፍላጎት እንደተጠበቀ ሆኖ የመረጡት የካፒታል ዕቃ ዓይነት በትክክል የሚፈለገውን የምርት ጥራትና ምርታማነት ለማምጣት

የሚያስችል ስለመሆኑ በተለያዩ ባለሙያዎች የማረጋገጥና የማማከር ስራ መስራት ተገቢ ይሆናል፡፡

በመሠረታዊነት የማምረቻ መሳሪያው ዝርዝር መግለጫ (Specification) ዝግጅት በኢንተርፕራይዞች መከናወን ያለበት ቢሆንም አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ራሳቸውን ችለው ለማዘጋጀት መቸገራቸው አይቀርም፡፡ በመሆኑም የተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች የማምረቻ መሳሪያ ፍላጎት ልየታና በማምረቻ መሳሪያዎች ዝርዝር መግለጫ ዝግጅት ላይ እገዛ የማድረግ ስራ በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ስራ አክሲዮን ማህበራት፣ በኢትዮጵያ ልማት ባንክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች፣ የአነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ልማቱን በሚመሩ የክልል ቢሮዎች/ኤጀንሲዎች፣ በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተሳታፊነት እንዲደገፍ ማድረግ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

2.3.2. የካፒታል ዕቃ ተጠቃሚዎች ልየታ

በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የተሰማሩ ወይም መሰማራት የሚፈልጉ ኢንተርፕርነሮች በዘርፉ የሚደረግላቸውን ድጋፍ እንደ እርሾ በመጠቀም በራሳቸው ላብ እና ክህሎት ለውጥ አመጣለሁ በሚል ቁርጠኛ መንፈስ ወደ ሥራ ገብተው በትክክልም የኢንተርፕራይዝ መሠረትነታቸውን የሚያስመሰክሩ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡ አዲስ ኢንተርፕራይዞቹ ሲቋቋሙና የማስፋፊያ ድጋፍ ሲደረግላቸው ጊዜያዊም ሆነ ቋሚ የስራ ዕድል መፍጠራቸው የማይቀር ጉዳይ ቢሆንም የድጋፉ መሰረታዊ ዓላማ ዛሬ ታይተው ነገ የሚዘጉ ተቋማትን እዚህም እዚያም የማበራከት ጉዳይ ሳይሆን አስፈላጊ ዘመናዊ የማምረቻ ማሽነሪ ፍላጎት ያላቸውን በመለየት ከሚመለከታቸው የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዲያገኙ በማድረግ በኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግሩ ዋነኛ ተዋናይ የሆኑ ኢንተርፕራይዞችን መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

ክፍል ሶስት

3 የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት አሰራር ሥርዓት

በካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ሰጪዎች የሚሰጡ የአገልግሎት ዓይነቶች፣ በተገልጋይ ኢንተርፕራይዞች መሟላት ስለሚገባቸው መስፈርቶች፣ የአቅራቢ ልየታና የውል

ስምምነቶች፣ የአከፋፈልና የእፎይታ ጊዜያት እና የካፒታል ዕቃዎች የኮሚሺኒንግ ስራዎች አተገባበር፣

3.1. የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ዓይነቶች

በአሁኑ ሰዓት በአገራችን የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ሥርዓትን እንዲተገብሩ በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጣቸው የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ንግድ ስራ አክስዮን ማህበራት ሲሆኑ በቀጣይ አገልግሎቱ እየሰፋ ሲሄድ ለተመሳሳይ አገልግሎት ፈቃድ ወስደው ወደ ስራው የሚገቡ ተቋማት መፈጠራቸው አይቀርም። ከካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ጋር በተያያዘ በእነዚህ ተቋማት እንዲተገበሩ በብሔራዊ ባንክ በኩል ፈቃድ የተሠጠባቸው የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ዓይነቶች የዱቤ ግዢ /Hire Purchase/ እና የፋይናንስ ኪራይ /Financial Lease/ ናቸው።

3.1.1 የዱቤ ግዢ / Hire Purchase/

የዱቤ ግዥ በካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ስራ አዋጅ ቁጥር 103/1990 በተፈቀደው መሰረት የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኪራይ ዓይነት ሆኖ በአዋጁ እንደተጠቀሰው የኪራይ ስምምነቱ የሚከተሉት ልዩ ባህሪያት ይኖሩታል፡-

ሀ/ እያንዳንዱ የኪራይ ክፍያ በተፈጸመ ቁጥር ለክፍያው ተመጣጣኝ በሆነ መቶኛ ልክ የባለቤትነት መብት እንዲሁም የመጨረሻው የኪራይ ክፍያ እንደፈጸመ ወዲያውኑ የካፒታል ዕቃው ሙሉ የባለቤትነት መብት ለተከራዩ የሚተላለፍለት መሆኑ፤

ለ/ ስምምነቱ በማናቸውም ወገን ያለጊዜው በሚቋረጥበት ጊዜ ከስምምነቱ የሚመነጭ የባለቤትነት መብቶችና ጥያቄዎች እልባት የሚያገኙበትን ሁኔታ ሁለቱ ወገኖች በስምምነታቸው ሊያካትቱ የሚገባ መሆኑ፤

ሐ/ ተከራዩ ለካፒታል ዕቃው የመድህን ዋስትና የመግባትና በየዓመቱ የማደስ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ፤

መ/ የውል እና የካፒታል ዕቃ ምዝገባ ወጪ የሚሸፈነው በተከራይ መሆኑ፤

3.1.2 የፋይናንስ ኪራይ /Financial Lease/

የፋይናንስ ኪራይ ስምምነቱ የሚከተሉት ልዩ ባህሪያት ይኖሩታል፡-

ሀ/ ተከራዩ የኪራይ ስምምነቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ሁሉ የካፒታል ዕቃውን በአግባቡ እንዲጠቀምበት የውል ስምምነት ይገባል፤ ተከራዩ በካፒታል ዕቃው ላይ ምንም አይነት የባለቤትነት መብት የለውም፤

ለ/ ስምምነቱ ውል የተገባበት ሙሉ ዋጋ በኪራይ ተከፍሎ የሚሸፈንበትና ሊሠረዝ የማይችል ሥምምነት ነው፤

ሐ/ የሥምምነቱ ጊዜ ሲያበቃ ሁለቱ ወገኖች ከተሥማሙ ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን የመግዛት ምርጫ ይኖረዋል፤ ካልተስማሙ ተከራዩ የካፒታል ዕቃውን ለአከራዩ ይመልሳል፤

መ/ ተከራዩ ለካፒታል ዕቃው መድህን የመግባትና ተገቢውን ዕድሳት በየወቅቱ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፤

ሠ/ የውል እና የካፒታል ዕቃ ምዝገባ ወጪ የሚሸፈነው በተከራይ መሆኑ፤

3.1.3 የምክር አገልግሎት

የዕውቀት እና የመረጃ ውሱንነት ላለባቸው ኢንተርፕራይዞች በስፔሲፊኬሽን ዝግጅት፣ ለተጀመረም ሆነ ላልተጀመረ ቢዝነስ አዋጪና ከደረጃ ዕድገታቸው ጋር የሚመጣጠኑ የማምረቻ ማሽኖች ከመለየት አንጻር ኩባንያዎቹ የቢዝነስ ዕቅድ አሞላልና ተመሳሳይ ተግባራት በባለሙያዎች ድጋፍ እና የምክር አገልግሎት ይሰጣቸዋል፡፡

3.2. አገልግሎት ለማግኘት የሚሟሉ ቅድመ-ሁኔታዎችና የሥራ መስኮች

ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች አገልግሎት ለማግኘት ማቅረብ የሚገባቸው መስፈርቶች እና እንደየ ዕድገት ደረጃቸው የሚሰማሩባቸው አዋጭ የሆኑ የማምረት ስራ ንኡሳን ዘርፎች እየለዩ የሚያቀርቡ ይሆናል፤

3.2.1 ኢንተርፕራይዞች ማሟላት የሚገባቸው ዋና ዋና መስፈርቶች

- የማምረት የስራ ዘርፍ ላይ የተሰማራ ወይም ለመሰማራት የፈለገ
- የንግድ ማህበር ከሆነ የመመስረቻና መተዳደሪያ ደንብ ኮፒ
- የተጠየቁት ማሽኖች ለመትከል በቂና መሰረተ ልማቱ የተሟላ ቦታ ማዘጋጀት
- በሚመለከተው አካል የጸደቀ የመስሪያ ቦታ የኪራይ ውል
- ቲን፣ የንግድ ምዝገባና የንግድ ስራ ፈቃድ
- የንግድ ዕቅድ ወይንም የአዋጭት ጥናት

- የሚፈለጉት የካፒታል ዕቃዎች ዝርዝርና(specification) እና ሞዴል
- ቅድመ ክፍያ/down payment/ ለመክፈል ዝግጁ የሆነ፤
- ለሚሰማራበት የማምረት ስራ የሥራ ማስኬጃ ያለው
- የድርጅቱ አባላት የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ኮፒ፣
- የግል ኢንተርፕራይዝ እና የንግድ ማህበር የአባላት የጋብቻ ወይም ያላገባ ሰርትፊኬተ ኮፒ
- የድርጅቱ አባላት በሙያው የሰለጠኑበት/ልምድ ካለ ማቅረብ
- የብድር ታሪክ መረጃ ካለ ከፋይናንስ ተቋማት ማቅረብ

3.2.2. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት የሚተገበርባቸው የማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች

መንግስት የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ልማቱን ለመደገፍ በመሰረታዊነት የሚከተሉትን ዓላማዎች ለሚያሳኩ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ቅድሚያ ሰጥቶ የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ያቀርባል፡፡

ሀ/ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግሩን የሚደግፉ፤

ለ/ ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶችን መተካት የሚችሉ፤

ሐ/ ወደ ውጭ ሃገራት ምርታቸውን በመላክ የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኙ፤

መ/ በአምራች ስራ መስክ ወደ ስራ ሲገቡ ሰፊ የስራ ዕድል መፍጠር የሚችሉ፤

ከላይ የተቀመጡት መሠረተ-ሐሳቦች እንደተጠበቁ ሆኖ የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት በሚከተሉት ንዑሳን የስራ መስኮች ለተሰማሩ ወይም መሰማራት ለሚፈልጉ ተገልጋዮች ይሠጣል፡፡

- አግሮፕሮሰሲንግ
- የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ማምረት፤
- የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ማምረት፤
- የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ሥራ፤
- የእንጨት ውጤቶች ማምረት፤
- የዕደ ጥበብ ውጤቶች ማምረት፤
- የኬሚካል ውጤቶች ማምረት፤
- የኮንስትራክሽን ግብዓት ማምረት፤
- የፕላስቲክ መልሶ መጠቀም/ሪሳይክሊንግ /ስራ እና ሌሎች የማምረት ስራ መስኮች

3.3 የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት

ከግንዛቤ በኋላ ኢንተርፕራይዞች የካፒታል ዕቃ ፍላጎት የሚገልጽ የተለዩ ህጋዊ አደረጃጀትን በማሟላት ማመልከቻ ካቀረቡ በኃላ ይያቂው ወደ ግዢ ሂደት ከመሻገሩ በፊት በኩባንያው ባለሙያዎች በስራ ቦታ የአዋጭነት ግምገማ/Bussiness Apraisal/ ይከናወናል፤

3.3.1 የካፒታል ዕቃ ፍላጎት ማመልከቻ ማቅረብ

- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ የኪራይ ጥያቄ ማመልከቻ ማቅረብ
- በመሰረታዊነት ኢንተርፕራይዙ ሊሰራው ያሰበውን የስራ ሁኔታ፣ የሚፈልገውን የካፒታል ዕቃ ዓይነትና ስፔሲፊኬሽን፣ የዋጋ መጠን፣ ወዘተ ማቅረብ፡፡

3.3.2 የአዋጭነት ግምገማ ማካሄድ

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ለመስጠት የቀረበው ቢዝንስ ፕላን በዋናነት የአዋጭነት ግምገማ ላይ ተመስርቶ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተቋም በኢንተርፕራይዙ በሥራ ቦታው በመገኘት ግምገማ ያካሂዳል

3.3.3 የካፒታል ዕቃ ግዢ ቅድመ-ሁኔታዎች

- ተከራይ የሚፈልገውን የካፒታል ዕቃ ዝርዝር መግለጫ /specification/ እና ሞዴል ማቅረብ፤
- ኢንተርፕራይዝ በዝርዝር መግለጫው መሠረት የሚገኝበትን ቦታ መግልጽ በተጨማሪም ተወዳዳሪ የሆኑ የማሽን አምራች ወይም አቅራቢዎችን መለየት

3.4 የካፒታል ዕቃ ዓይነትና የማሽን አምራች ወይም አቅራቢዎችን ስለመለየት

ሀ/ በሀገር ውስጥ ዕቃዎችን አምርተው የሚያቀርቡ

- የውጭ ምንዛሬን በማስቀረት የሃገር ውስጥ አቅምን መጠቀም ያስችላል
- የማሽን አምራች ኢንተርፕራይዞች በተጠናከሩ ቁጥር በጥራት፣ በዋጋና በአቅርቦት የመወዳደር አቅም እየፈጠሩ እንዲሄዱ ያደርጋል፤
- የአገር ውስጥ ማሽን አምራች ኢንተርፕራይዞችንም በግዥ ሂደቱ እያሳተፉ እያበረታቱ መሄድን ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡

- የአገር ውስጥ ማሽን አምራች ኢንተርፕራይዞች የሚያመርቷቸው ማሽኖች በተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች ፍላጎት መሰረት በጥራት እና በብዛት እንዲያመርቱ አቅማቸው እንዲገነቡ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡
- አነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች አገር ውስጥ የሚመረቱ በጠየቁት ስታንዳርድ የሚመረቱ ማሽነሪዎች ላይ ከጊዜ እና ከዋጋ አንጻር ባለው ጠቀሜታ ምክንያት ትኩረት እንዲያደርጉ ማድረግ

ለ/ አስመጪ አቅራቢዎች

- በሀገር ውስጥ የማይመረቱ ሆነው የሚከራየው ኢንተርፕራይዝ ፍላጎትን መሰረት ባደረገ በሚቀርበው ዝርዝር መግለጫ (specification) መሠረት እንዲያቀርቡ ማድረግ ሌላው አማራጭ ነው፡፡

ሐ/ የውጭ አገር ማሽን አቅራቢ/አምራች

- በሀገር ውስጥ የማይመረቱና መገኘት የማይችሉ የካፒታል ዕቃዎች በሚጠየቁበት ጊዜ ይሄው እየተረጋገጠ ህጋዊ ፈቃድና ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያላቸውን ተቋማት በግዥ መመሪያው መሠረት በመጋበዝ የካፒታል ዕቃን እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡
- አጠቃላይ የማሽነሪ አቅርቦቱን በተመለከተ በአከራዩ፤ ተከራይና በአቅራቢው መካከል ሙሉ በሙሉ በተደረገ ስምምነት የሚፈጸም ይሆናል

3.5 የካፒታል ዕቃ ኪራይ ውል ስምምነት ስለማድረግ፤

3.5.1. በቢዝነስ ፕላን ወይም በአዋጭነት ጥናት መሰረት የማምረቻ መሳሪያ ጥያቄው ተገምገሞ ከጸደቀ በኂላ ተከራይና አከራይ የካፒታል ዕቃ ኪራይ ውል ስምምነት ያደርጋሉ፡፡ የውል ስምምነት ሰነዱ በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ የፋይናንስ ተቋማቱ ተዘጋጅቶ ይቀርባል፡፡

3.5.2 በአቅራቢ እና በአከራይ መካከል የካፒታል ዕቃ አቅርቦት ስምምነት ይፈጸማል፤

3.5.3. እንደ አስፈላጊነቱ በአከራይ ተከራይና አቅራቢ መካከል የሚደረግ የሶስትዮሽ ውል ስምምነት ይደረጋል

3.6 የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኪራይ ክፍያ እና የሊዝ ዘመን አወሳሰን ሥርዓት

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት የኪራይ ክፍያ የማሰባሰብ ተግባር በወቅቱና በተገባው ውል መሠረት መከናወን የሚገባው ሲሆን የአከፋፈል ስርዓቱ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ/ የኪራይ ክፍያ ጊዜ

የክፍያ ጊዜን በተመለከተ በሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል ሊወጡ የሚችሉ መመሪያዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በዋናነት እንደየሥራው ዓይነት፣ የኪራይ መጠንና የመመለስ አቅም እንዲሁም ካፒታል ዕቃው ሊኖረው በሚችለው የአገልግሎት ዘመን ላይ ተመስርቶ የሚወሰን ሆኖ ከፍተኛው የመክፈያ ጊዜ እስከ አስር (10) ዓመት ይሆናል፡፡

የኪራይ ክፍያ ሥርዓቱ እንደ ስራው ዓይነት አከራይና ተከራይ በሚያደርጉት ስምምነት መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይችላል፡፡

የሊዝ ክፍያ አመላለስ እንደየስራው ዓይነት አከራይና ተከራይ በሚያደርጉት ስምምነት መሰረት ተግባራዊ የሚደረግ ሆኖ በየወሩ፤ በየሶስት ወሩ ወይም በየስድስት ወር ይሆናል፡፡

ለ/ የኪራይ/የአገልግሎት ክፍያ

- የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ለሚከራዩት ዕቃ እንዲከፍሉ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የኪራይ ምጣኔውንና አከፋፈሉን በተመለከተ የመወሰን ኃላፊነቱ የአከራዩ ሆኖ ተከራይና አከራይ አስቀድመው በሚገቡት ውል ውስጥ ተካቶ እንዲፈርሙበት ይደረጋል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ አገር በብሔራዊ ባንክ በኩል በወለድ ምጣኔ ላይ የሚደረጉ ማስተካከያዎች በሚኖሩበት ወቅት አከራዩ አስቀድሞ ባስቀመጠው የኪራይ ምጣኔ ላይ ማስተካከያ ሊያደርግ ይችላል፡፡
- በተከራዩ ላይ የኪራይ ክፍያ መሠላት የሚጀምረው የካፒታል ዕቃው ተተክሎ ከተሞከረ በኋላ በአከራይና በተከራዩ መካከል ርክክብ ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ ይሆናል፤

ሐ/ የእፎይታ ጊዜ

የእፎይታ ጊዜ እንደ የኢንተርፕራይዞቹ ዓይነትና እንደሚያመርቷቸው ምርቶች የሚለያይ ሆኖ ማሽኑ ተተክሎ የሙከራ ምርት በማምረት ርክክብ ከተፈጸመበት ጊዜ አንስቶ ከአራት እስከ ስድስት ወራት የሚደርስ የእፎይታ ጊዜ የሚሠጣቸው ሲሆን ይህም በአከራይና በተከራይ መካከል በሚደረገው ስምምነት መሰረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

መ/ የካፒታል ዕቃ ግዢ ስለማከናወን

I. በኢንተርፕራይዙ ፍላጎት በተለየው ማሽን አምራች/አቅራቢ መሰረት ተከራይ ቅድመ-ክፍያ መፈጸሙ ከተረጋገጠ በኋላ በተዘጋጀውና ተከራይና አከራይና አቅራቢ በተስማሙበት ዝርዝር መግለጫ /specification/ መሠረት ለአቅራቢው የግዢ ወይም የስራ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

II. በዚህ ወቅት የካፒታል ዕቃውን የሚያስረክብበት ቦታ በግልጽ መገለጽ ይኖርበታል፡፡

III. ስለ ካፒታል ዕቃው ደህንነት፣ የዋስትና ጉዳይና ከግዢ በኋላ ያሉ አገልግሎቶችና ጥገና ስራዎች አቅራቢና አከራይ በጋራ በሚገቡት ውል መሠረት ይተገበራል፡፡

ሀ/ በግዢ ሂደት የሚከናወኑ ተግባራት፡-

I. የካፒታል ዕቃ ተከራይ የራሱን ፍላጎት መሠረት በማድረግ የካፒታል ዕቃውንና የካፒታል ዕቃ አቅራቢን በነፃነት የመምረጥ መብት ቢሰጠውም አከራዮች ለኪራይ የሚውለው የካፒታል ዕቃ እንደ ዋስትናም ስለሚያገለግል ጥራቱን በሚወስነው የስፔስፊኬሽን ዝግጅት ስራ ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ሙያዊ ዕገዛ ማድረግና ማማከር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ አቅራቢውን የማወዳደር ተግባር የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማቱ ይሆናል፡፡

II. አቅራቢዎችና የማሽን አምራች ድርጅቶች በኢንተርፕራይዙና አከራዩ በኩል በተደረገ ስምምነት በቀረበላቸው ስፔስፊኬሽን መሰረት የካፒታል ዕቃውን ከነመለዋወጫ እና አክሰሰሪዎች ማቅረብ የሚጠበቅባቸው ሲሆን በአከራዩና በአቅራቢ ተቋሙ መካከል የተደረገው የውል ስምምነት የተከላና የሙከራ የስልጠና ስራን ባካተተ አግባብ እንዲሆን ይደረጋል፤

III. ተከራዩ ቅድመ-ክፍያ ከከፈለ በኋላ የካፒታል ዕቃውን ለመረከብ የሚወስደው ጊዜ ከ6 ወራት መብለጥ የለበትም፡፡

IV. የካፒታል ዕቃ የኪራይ መጠን

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለአንድ ተከራይ በአንድ ጊዜ ሊቀርብ የሚችለውን የካፒታል ዕቃ ኪራይ መጠን ለመወሰን ባወጣው መመሪያ መሠረት፡-

- በክልሎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች ከፊል ወይም ሙሉ ባለቤትነት የሚቋቋሙ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተቋማት ለአንድ ተከራይ በኪራይ ማቅረብ የሚችሉት የካፒታል ዕቃ ዋጋ ከአክሲዮን ማህበሩ ካፒታል ከ2.5 በመቶ የማይበልጥ ይሆናል፡፡
- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለአንድ ተከራይ የሚሰጠው የኪራይ መጠን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተቀመጠው መመሪያ መሠረት የአነስተኛ እና የመካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ካፒታልን 80 በመቶ መብለጥ የለበትም፤
- አሁን የሚሰራበት የኪራይ ጣሪያ ከላይ እንደተገለጸው ሆኖ በቀጣይ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በአከራዮች ለአንድ ተከራይ በአንድ ጊዜ ሊቀርብ የሚችለውን የኪራይ መጠን አስመልክቶ የሚያደርገው ማሻሻያ በሚኖርበት ጊዜ በማሻሻያው መሠረት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

3.7. የካፒታል ዕቃ ማጓጓዝና ርክክብ ስለማከናወን

ሀ/ የካፒታል ዕቃ ማጓጓዝ

የካፒታል ዕቃ ርክክብ ስርዓቱ የተከራይ የማምረቻ ቦታ ድረስ እንዲሆን የሚደረግ ሲሆን አቅራቢ በራሱ ማጓጓዣ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ለ) በርክክብ ወቅት መታየት ያለባቸው

- የካፒታል ዕቃው በተጠየቀው በስፔስፊኬሽን እና ሞዴል መሰረት የቀረበ መሆኑን፤
- የተፈበረከበት መለያ ቁጥሩ ትክክል መሆኑን፤
- በውሉና በስምምነቱ መሠረት አክሰሰሪና መለዋወጫ መኖራቸውን በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማቱ ባለሙያዎች፣ በአቅራቢው እና በኢንተርፕራይዙ በጋራ በማረጋገጥ ርክክብ ይካሄዳል::

ሐ) ለተጠቃሚ ኢንተርፕራይዝ ማስረከብ

- በመስሪያ ቦታው የደረሱ የካፒታል ዕቃዎች በአቅራቢ እና በአከራይ በተገባው ውል መሰረት የገቡት ማሽኖች የኩባንንያው ንብረት ክፍል ገቢ ያደርጋል
- ኢንተርፕራይዞቹ በመረጡት ስፔሲፊኬሽን እና ሞዴል መሆኑን በማረጋገጥ ከአከራይ ይረከባሉ፡፡

3.8. የካፒታል ዕቃዎች ኢንሹራንስ መግባት፣

የካፒታል ዕቃው በአዋጅ ቁጥር 103/1990 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1(መ) እና 3(ሐ) መሰረት ኢንሹራንስ እንዲገባለት ይደረጋል። በዚሁ መሰረት የኢንሹራንስ ወጪው በተከራይ የሚሸፈን ይሆናል።

I. ይህ ተግባር የሚከናወነው በርክክብ ወቅት የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ በጋራ ከሚሰራው የኢንሹራንስ ኩባንያ ጋር ይሆናል።

II. ለማምረቻ መሳሪያዎች የሚገባው ኢንሹራንስ ዓይነት እንደ ማምረቻ መሳሪያው የተጋላጭነት ሁኔታ በአከራይና በተከራይ መካከል በሚደረገው ስምምነት መሰረት ይፈጸማል።

III. በየዓመቱ የሚደረገው የካፒታል ዕቃዎች የመድን ሽፋን ዕድሳትም በኢንተርፕራይዙ ይከናወናል።

IV. ተከራዩ ተከታትሎ ይህን ማድረግ ካልቻለ በሚያደርጉት ስምምነት መሰረት አከራዩ ክፍያውን በመክፈል የኪራይ ዋጋው ላይ በማሰብ የሚያስከፍል ይሆናል።

3.9 የካፒታል ዕቃ ተከላ፣ ሙከራ እና የአጠቃቀም ሥልጠና

I. የካፒታል ዕቃ ለተጠቃሚዎች ከመተላለፉ በፊት በአቅራቢው ድርጅት በኩል የተከላና የሙከራ ምርት ማምረት ተግባር መከናወኑን በአከራዩና ተከራዩ የሚረጋገጥ ይሆናል።

II. የካፒታል ዕቃ አቅራቢው በውሉ መሠረት ስለ ካፒታል ዕቃው አጠቃቀም፣ ጥገና እና ሰርቪስ ስልጠና ይሰጣል።

3.10. የካፒታል ዕቃ ምዝገባ እና የውል ምዝገባ ስለማከናወንና

ሀ/ የካፒታል ዕቃ ምዝገባ

I. በኪራይ የሚቀርቡት የካፒታል ዕቃዎች በአከራዩ ስም የሚገዙ ሆኖ ሕጋዊ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ እና በምዝገባ ወቅት የተሰጠው መለያ ቁጥር እንዲኖረው ተደርጎና ስልጣን በተሰጣቸው አካላት ማለትም በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክና በንግድ ቢሮ መመዝገባቸውን ይረጋገጣል፤

II. የካፒታል ዕቃ ምዝገባ የሚከናወነው ያለበትን እዳ ከፍሎ ሳይጨርስ የካፒታል ዕቃውን እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ እንዲሁም በብድር ዋስትና እንዳይያዝ ለማድረግ ነው፡፡

III. የካፒታል ዕቃውን ያለ ካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማቱ ዕውቅና ከቦታ ወደ ቦታ ማዘዋወር አይቻልም፡፡

ለ) የውል ምዝገባ

በአከራይና በተከራይ መካከል የተፈጸመው ውል በንግድ ቢሮ እንዲመዘገብ ይደረጋል፡፡

3.11. የካፒታል ዕቃ አያያዝ፣ ጥገናና ዕድሳት ስለማድረግ

I. በካፒታል ዕቃ ኪራይ ውሉ መሠረት ንብረቱን የሚጠቀምበት ተከራዩ በመሆኑ የካፒታል ዕቃውን በጥንቃቄ ይዞ የመጠቀም ሃላፊነት ይኖረዋል፣

II. ተከራይ ከዋራንቲ ውጪ ተከታታይ ጥገናና እድሳት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ አውቶትና ተረድቶት በኪራዩ ውል ውስጥ ተካቶ ደንበኛው እንዲፈርም ይደረጋል፤

III. ተከራዩ የተሰጠውን የካፒታል ዕቃ በአጠቃቀም ማኑዋሉ መሠረት መጠቀም አለበት፡

IV. የዋስትና ጊዜ ከማብቃቱ በፊት ለሚደረገው ጥገና የማሽኑ አምራች ፋብሪካው ተግዳሮት ከሆነ አቅራቢው በራሱ የሚያከናውን ሲሆን የዋስትና ጊዜ ካበቃ በኋላ ለሚደርሱ ብልሽቶች ለጥገናና ዕድሳት የሚወጣው ወጪ በተከራዩ የሚሸፈን ይሆናል፡፡ ይህም በውሉ ላይ በግልጽ ተካትቶ ደንበኛው እንዲፈርም ይደረጋል፡፡

V. የጥገናና እድሳት ደረጃው ቀላል ከሆነ ተከራዩ ጥገናና እድሳት የሚደረግበትን ቦታ፣ ለጥገናና እድሳቱ የሚጠይቀውን ወጪና በየትኛው ቦታ ጥገናና እድሳት እንደሚደረግለት ማሽን ከቦታው ከማንቀሳቀሱ በፊት ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ በወቅቱ ማሳወቅ አለበት::

VI. ከባድ የሆነ ጥገናና ዕድሳትን በተመለከተ አከራዩና ተከራዩ በጋራ በሚመርጡት ቦታ እንዲከናወን የሚደረግ ሲሆን የሚጠገነው ማሽን ከቦታው ከማንቀሳቀሱ በፊት ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ በወቅቱ ማሳወቅ አለበት::

3.12. የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ስለማከናወን

የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ማሽኑ ተተክሎ ስልጠና መሰጠቱንና ሥራ መጀመሩን ተከራይ ዕዳው እስከሚዘጋ ድረስ መከታተል አለበት፡፡ የካፒታል ዕቃውን ካከራየ በኂላ በትክክል ስራ መጀመሩን በተመዘገበ ቀን ወርና ዓ.ም በመፈራረም ወደ ሥራ ማስገባትና ለሚፈለገው ስራ መዋሉን ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

3.13. የአከራይና ተከራይ ውል የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎችና ቀጣይ የሚወሰዱ እርምጃዎች

3.13.1. የካፒታል ዕቃው ስምምነት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፡-

I. አከራይና ተከራይ ተስማምተው የስምምነት ውሉን ሲያቋርጡ፤

II. በተከራይ ፍላጎት የኪራይ ስምምነቱ ሊቋረጥ ይችላል፡ ሆኖም ግን ተከራይ ከስምምነት መቋረጥ በፊት የነበሩ ወጪዎችንና የጉዳት ካሳ መክፍል ግዴታ ይኖርበታል፡፡

III. ተከራይ በገባው ውል መሰረት የካፒታል ዕቃውን ለታለመለት ዓላማ ሳያውል ከቀረ አከራይ በጋራ ውል መሰረት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስምምነቱ ሊቋረጥ ይችላል፡፡

IV. ተከራዩ የካፒታል ዕቃው በተላለፈለት ወቅት በታዘዘው ስፔሲፊኬሽን ሞዴል መሰረት ካልሆነ

V. አከራይ በገባው ውል መሠረት የካፒታል ዕቃውን ማቅረብ ካልቻለ፤

VI. ተከራይ ከአከራይ ጋር በገባው ውል መሠረት ክፍያ ሳይፈጽም ሲቀር፤

VII. የተከራይ የኪራይ ውል ጊዜው ሲያበቃ፤

3.13.2. ከአከራይና ተከራይ ውል መቋረጥ በኂላ የሚወሰዱ እርምጃዎች

I. በተከራይ ፍላጎት የኪራይ ስምምነቱ ሲቋረጥ ከስምምነት መቋረጥ በፊት የነበሩ ወጪዎችንና የጉዳት ካሳ ተከራይ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡

II. በአከራይ በመልሶ መረከብ የተወሰዱ የካፒታል ዕቃዎች ለሌላ ተከራይ መልሶ ማከራየት ወይም መሸጥ ይችላል፤

III. ከስምምነት መቋረጥ በፊት ተከራዩ ለከፈለው ቅድመ-ክፍያ በውል ላይ በሚገለጸው መሰረት ወለድ በማሰብ በተጨማሪ በተስማሙበት አግባብ የጉዳት ካሳ ለተከራይ ይከፍላል፡፡

IV. በተገባው ውል መሰረት ተከራይ የክፍያ ግዴታውን የማይወጣ ከሆነ የመልሶ መረከብ/Repossession/ እንደ መጨረሻ አማራጭነት ይወሰዳል፤

V. በመልሶ መረከብ የተወሰዱ የካፒታል ዕቃዎች ተከራይተው ወይም ተሸጠው ተከራይ መክፈል የሚገባውን ክፍያ መሸፈን ካልቻለ በህግ እንዲጠየቅ ይደረጋል፤

3.14. የካፒታል ዕቃ አቅራቢ እና የአከራይ ውል የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎችና ቀጣይ የሚወሰዱ እርምጃዎች

3.14.1. የካፒታል ዕቃው አቅራቢና የአከራይ ስምምነት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፡-

I. የቀረበው የካፒታል ዕቃ በታዘዘው ስፔሲፊኬሽንና ሞዴል መሰረት ሳይሆን ሲቀር

II. አከራይ በገባው ውል መሠረት በጊዜ የካፒታል ዕቃውን ማቅረብ ካልቻለ፤

3.14.2. ከአቅራቢና አከራይ ውል መቋረጥ በኋላ የሚወሰዱ እርምጃዎች

I. አቅራቢ በውሉ መሠረት በጊዜ ካላቀረበ ውሉ ላይ በተገለጸው ቅጣት መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

II. በስህተት የገባውን ማሽን በራሱ ወጪ ወደ ራሱ በመመለስ በውሉ ላይ በተገለጸው ቅጣት መሰረት ይፈጸማል፤

III. አቅራቢ በተገባው ውል መሰረት ማስረከብ ካልቻለ፣

ክፍል አራት

4. የፈጻሚ፣ አስፈጻሚ እና የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

ከዚሁ ጎን ለጎን ኢንተርፕራይዞቹ ማሟላት የሚገባቸውን ቅድመ-ሁኔታዎች ለማሟላት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የመንግስት ድጋፎችና አገልግሎቶች በመስጠት ረገድ ድርሻ ያላቸው አካላትም ተለይተው ተገቢውን ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ አስፈላጊ ነው፤

4.1. ፈጻሚ አካላት

አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ከካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ጋር በተያያዘ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች እንዲቀረፉ የፈጻሚ አካላት ሚና አስፈላጊ በመሆኑ ይህንን ተልእኮ ለመወጣት የሚያስችል ተግባርና ሃላፊነት ተዘርዝረዋል፤

4.1.1 የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት

I. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት የድጋፍ ማዕቀፎች እንዲቀረጹ ያደርጋል፤

II. በኢንተርፕራይዞች ሊፈለጉ የሚችሉ የካፒታል ዕቃዎችን ዝርዝር ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ይለያል፣ ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት በግብዓትነት እንዲያገለግል ያደርጋል፤

III. የካፒታል ዕቃ ዝርዝር መግለጫ /specification/ ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር ያሠባስባል፤ ያጠናቅራል ያሠራጫል፤

IV. የካፒታል ዕቃ ተጠቃሚ የሚሆኑ/የሆኑ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የክላስተርና መሰረተ-ልማት አቅርቦት ድጋፍ እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው ጋር በቅንጅት ይሠራል፤

V. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦቱን በዓይነት ወይም በገንዘብ ሊደግፉ ከሚችሉ ሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ጋር በመስራት እገዛና ድጋፍ እንዲያደርጉ ያስተባብራል፤

VI. የካፒታል ዕቃ ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች የሀገር ውስጥና የውጭ ገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ይሠራል፤

VII. የዘርፉን የልማት ችግሮች ለመለየትና ለመፍታት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያከናውናል፣ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በመቀመርና ለተጠቃሚዎች በማሰራጨት አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

VIII. አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የሚታይባቸውን የማምረቻ መሳሪያዎች ክፍተት በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት እንዲሸፈን ያደርጋል፤

IX. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት አፈጻጸም ያለበትን ደረጃ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ይከታተላል፤ ግብረ መልስ ይሰጣል፤

X. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማትን አቅም የመገንባት ሥራ ያከናውናል፤

4.1.2 የአምራች ኢንዱትሪ ልማት ኢንስቲቲዩት

I. የአነስተኛ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ልማቱ ከካፒታል ፋይናንስ አቅርቦት ጋር ተያያዞ ያሉበትን ዋና ዋና ማነቆዎች በጥናት ይለያል፤

II. በክፍተት ላይ ተመስርቶ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን ለሚደግፉ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በቴክኖሎጂ ኩረጃ፣ በምርት ጥራት አጠባበቅ፣ በጥሬ ዕቃ አጠቃቀም፣ በገበያ፣ በምርታማነት ማሳደግ፣ በቴክኒክ ክህሎት ወዘተ ላይ በመመስረት የተግባር ላይ ስልጠና ይሠጣል፤ በተከታታይ በመደገፍ አቅማቸውን ይደግፋል፤

III. የአነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የሚፈልጓቸውን ግብዓቶች በሚፈለገው ጥራት ደረጃና በተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ሙያዊ ዕገዛ ያደርጋል፤ ትሥሥር በመፍጠር ሂደትም ይሳተፋል፤

IV. በየሙያ መስኩ ለኢንተርፕራይዞች የሚያስፈልጉ ማምረቻ መሳሪያዎችን በመለየት ስፔሲፊኬሽን የማዘጋጀት ስራ ላይ ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል፤

V. ከቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማቱ የመደገፍ ከአቅም በላይ የሚሆኑ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሲኖሩ ክፍተትን መሰረት ያደረገ ድጋፍ ይሠጣል፤

4.1.3 በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሠጣቸው የካፒታል ዕቃ አከራይ ተቋማትና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ

I. ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት አሰራር የሚያገለግሉ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያዎችና ማኑዋሎችን ያዘጋጃሉ፣ በፈጻሚ፣ በአስፈጻሚ እና በባለድርሻ አካላት ተገቢው ግንዛቤ ተይዞባቸው እንዲተገበሩ ይሠራሉ፤

II. ከሚመለከታው አካላት ጋር በመቀናጀት በዘርፉ ተሰማርተው የሚገኙ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችም ይሁኑ መሰማራት የሚፈልጉ የህብረተሰብ ክፍሎች ስለካፒታል ዕቃ ኪራይ አቅርቦት ተገቢውን ግንዛቤ እንዲጨብጡ ያደርጋሉ፤

III. ከተፈጠረላቸው ግንዛቤ በመነሳት ቢዝነስ ፕላን የሚያቀርቡ ኢንተርፕራይዞችን ጥያቄ ተቀብሎ ተገቢውን ግምገማ ፈጥኖ በማካሄድ ውጤቱን ጥያቄው በቀረበ ከአስራ አምስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለኢንተርፕራይዞቹ ያሳውቃሉ፤

IV. ቢዝነስ ፕላናቸው ተገምግሞ የጸደቀላቸው ኢንተርፕራይዞች አስፈላጊ ቅድመ-ሁኔታዎችን ፈጥነው እንዲያሟሉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋሉ፤

V. ኢንተርፕራይዞች ያቀረቡትን የካፒታል ዕቃ ዝርዝር መግለጫ /Specification/ በጥልቀት በማየት በገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የማማከርና ሙያዊ ድጋፍ የመስጠት ስራ ያከናውናሉ፤

VI. የሚፈለገውን ቅድመ-ሁኔታ ላሟሉ ኢንተርፕራይዞች የሚፈልጉትን የካፒታል ዕቃ ከስድስት ወራት ባለበለጠ ጊዜ ውስጥ እንዲቀርብላቸው በማድረግ ተተክሎና ተሞክሮ ለኢንተርፕራይዞች በውል እንደተላለፍ ያደርጋሉ፤

VII. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞችን ለውጤታማነታቸው የሥራ እንቅስቃሴአቸውን ይከታተላሉ፤ ይደግፋሉ፤ የካፒታል ዕቃዎችን አያያዝና ደህንነት ይከታተላሉ፣ ክፍያን ይሰበስባሉ፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላሉ፤

4.10.1. የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት

I. ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ የሚያስፈልጋቸውን ጥሬ ዕቃ ያቀርባሉ እንዲቀርብ ያመቻቻሉ፤

II. ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞቹ ያመረቷቸውን ምርቶች ለተለያዩ ድርጅቶች በግብዓትነት እንዲቀርብ ያመቻቻሉ

III. ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞቹ ያመረቷቸውን ምርቶች ለተለያዩ ተጠቃሚዎች እንዲቀርብ ያመቻቻሉ፤

4.1.5 በክልልና በከተማ አስተዳደር ደረጃ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ልማቱን የሚያስተባብሩ ኤጀንሲዎች እና ቢሮዎች

I. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦቱ በቅንጅት የሚመራበት አሰራር ይዘረጋል፤ ተግባራዊም ያደርጋሉ፤

II. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦትን በተመለከተ ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች እና ለተለያዩ የህብርተሰብ ክፍሎች ግንዘቤ ይፈጥራል፤ ተጠቃሚዎችን ይመለምላሉ፤

III. የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ጥያቄ ያቀረቡ ኢንተርፕራይዞች ማሟላት የሚጠበቅባቸውን ከንግድ ዕቅድ ዝግጅት፣ ከማምረቻ ማዕከላትና መሰረተ-ልማት አቅርቦት ወዘተ ጋር የተያያዙ ቅድመ-ሁኔታዎች በሙሉ እንዲያሟሉ ድጋፍ ይሰጣል፤ ክፍተቶች ሲኖሩም ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋሉ፤

IV. ቅደመ-ሁኔታዎችን ያሟሉ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ቅድመ-ክፍያ ባስገቡ ከስድስት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የማምረቻ መሳሪያው እንዲመጣላቸው ክትትል ያደርጋሉ፤

V. በዘርፉ ልማት ሚና ያላቸውን አካላት በማቀናጀት ሁሉም ፈጻሚ አካላት ባሉበት የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦቱን አፈፃፀም በመገምገም የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፤ይከታተላል፤ ግብረ መልስ ይሰጣሉ፤

VI. የካፒታል ዕቃ ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች የገበያ ትስስር በሚያገኙበት ሁኔታ ላይ ድጋፍ ያደርጋሉ፤

VII. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ተጠቃሚ የሆኑ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን የማሽነሪ ኪራይ ክፍያ በገቡት ውል መሰረት እንዲመለስ ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋሉ

VIII. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ተጠቃሚ የሆኑ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን በኪራይ የወሰዱትን ማሽነሪ በቅርበት በመከታተል እንዳይሸጥ፣ እንዳይለወጥና ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋሉ

IX. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተርፕራይዞችን መረጃ በማጠናቀር ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤

X. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አጠቃቀምን አስመልክቶ የተሻለ ተሞክሮ ያላቸውን ኢንተርፕራይዞች ተሞክሮ በመቀመር ለሌሎች የማስፋት ሥራ ይሠራል፤

4.1.6 የክልል/የከተማ/ወረዳ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኤጀንሲ /ቢሮ/ተቋማት

I. የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን ክፍተት መሰረት በማድረግ በተዘጋጁ የሥልጠናና የቴክኖሎጂ ልማት ማዕቀፎች መሰረት ድጋፍ ያደርጋል፤

II. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ለኢንተርፕራይዞቹ የሚያገለግሉ የካፒታል ዕቃዎች ዝርዝር መግለጫ /Specification/ ያዘጋጃል፤ በኢንተርፕራይዞች ተዘጋጅተው በሚቀርቡትም ላይ ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል፤ ያማክራል፤

III. የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን በማምረቻ ቦታዎች ከካይዘን ኢንስቲቲዩት ጋር የካይዘን ትግበራ ያደርጋል፣ በየጊዜውም ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

IV. በኢንተርፕራይዞች ተፈላጊ የሆኑ የማምረቻ መሳሪያዎች በአገር ውስጥ በጥራት የሚመረቱበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ከቴክኖሎጂ ኩረጃና አብዢ ኢንተርፕራይዞችን ከመፍጠር አንጻር ይሠራል፤

V. ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የተገዙ ማሽኖች ተከላና ሙከራ በሚደረግበት ጊዜ ተሳትፎ ያደርጋል፤ ርክክብ ከመፈጸሙ በፊት ማሽኖቹ በስፔሲፊኬሽን መሰረት መገዛታቸውንና ተሞክረው በትክክል የሚሠሩ መሆኑን የማረጋገጥ ስራ ላይ ይሳተፋል፤

VI. ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ስለካፒታል ዕቃ አጠቃቀም፣ አያያዝና ጥገና ሥልጠናና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤

VII. በንግድ ዕቅድ እና የአዋጭነት ጥናት አዘገጃጀት ላይ ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ስልጠና ይሠጣል፤ በሚያዘጋጁበትም ወቅት ሙያዊ ዕገዛ ያደርጋል፤

4.1.7 የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ማህበራት

I. አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ከማምረቻ ቴክኖሎጂዎች አኳያ ያሉባቸውን ችግሮች አስመልክቶ ጥናት ያደርጋል፤ የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት አሰራሩን አስመልክቶ ኢንተርፕራይዞች ግንዛቤ እንዲፈጠርላቸው ያደርጋል፤

II. የኢንተርፕራይዞቹ የምርት ጥራት ደረጃ ከፍ እንዲል አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤ የግብዓትና የገበያ ችግሮቻቸውን በተደራጀ አግባብ እንዲፈቱ ድጋፍ ያደርጋል፤

III. አነስተኛ መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በየስራ ዘርፋቸው የሚደራጁበትን እና የሚጠናከሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

4.1.8. የሥራ ማስኬጃ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት

I. ለጥሬ ዕቃና ለተለያዩ ወጪዎች የስራ ማስኬጃ የሚፈልጉ የካፒታል ዕቃ ኪራይ ተጠቃሚ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን ብድር ማመቻቸት

II. ከካፒታል ዕቃ አቅራቢ ተቋማት ጋር በመቀናጀት የስራ ማስኬጃና የካፒታል ዕቃና የገንዘብ ብድር ተጠቃሚ የሆኑ ደንበኞች የኪራይ ክፍያቸው በወቅቱ እንዲመልሱ ጥረት ማድረግ፤

4.1.9 የወጣቶችና የሴቶች አደረጃጀቶች፤

I. ስለተዘረጋው የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ድጋፍ ለወጣቶች እና ለሴቶች ተገቢውን ግንዛቤ በማስጨበጥ የድጋፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው ጋር በቅንጅት ይሠራሉ፤

II. የካፒታል ዕቃ ሊዝ ፋይናንስ ተጠቃሚ የሆኑ ወጣቶችና ሴቶች ወደ ስራ መግባታቸውንና የክፍያ ግዴታቸውን በአግባቡ እየተወጡ መሆኑን ይከታተላል፤ ይደግፋል፤

4.2 አስፈጻሚ አካላት

አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ከካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ጋር በተያያዘ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች እንዲቀረፉ የአስፈጻሚ አካላት ሚና አስፈላጊ በመሆኑ ይህንን ተልእኮ ለመወጣት የሚያስችል ተግባርና ሃላፊነት ተዘርዝረዋል፤

4.2.1. ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

I. የዘርፉን ልማት ለማፋጠን የሚረዱ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ሥርዓቶችን እና አሰራሮችን በማጥናት ለመንግሥት አቅርቦ ያስወስናል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

II. በየደረጃው የሚገኙ አስፈጻሚ አካላት የካፒታል ዕቃ አቅርቦቱን በማሳለጥ የዘርፉን ልማት እንዲደግፉና በባለቤትነት እንዲፈጽሙ ያስተባብራል፤ አቅማቸው እንዲገነባ ያደርጋል፤

III. በዘርፉ ልማት ሚና ያላቸውን አካላት በማቀናጀት ሁሉም ፈጻሚ አካላት ባሉበት የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ በማካሄድ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፤

IV. የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ከከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች ጋር በግብዓትና በገበያ ትስስር የሚፈጥሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

4.2.3 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

I. የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ሕጎችና መመሪያዎችን በማዘጋጀት እንዲተገበሩ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

II. ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት የስራ ፈቃድ ይሰጣል፣ የተቋማቱን ሥራዎች ያስተባበራል፤ ያቀናጃል፤

III. የሌሎች ሀገራትን ምርጥ ተሞክሮ በመቀመርና ተሞክሮውን በማሠራጨት አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

IV. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማትን አቅም ይገነባል፡፡

V. ለአነስተኛና መካከለኛ ማፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ የሚተላለፉ የካፒታል ዕቃዎች በብድር ዋስትና እንዳይያዙ ምዝገባ ያደርጋል፤

VI. የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦቱን አፈጻጸም ይገመግማል፤ ግብረ-መልስም ይሠጣል፤

4.2.2. ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር

I. ለአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የሚቀርቡ የካፒታል ዕቃዎችን ይመዘግባል፤ የባለቤትነት ማረጋገጫ ይሠጣል፤

II. ስለተመዘገቡት የካፒታል ዕቃዎችና የካፒታል ዕቃ ኪራይ ስምምነቶች የመረጃ ስርዓት ይዘረጋል፣ የተሟላ መረጃ ይይዛል፤ እንዲያዝም ያደርጋል፤

III. የካፒታል ዕቃዎችና የካፒታል ዕቃ ኪራይ ስምምነቶች ምዝገባ እንዲከናወን አግባብ ላለው አካል እንዳስፈላጊነቱ ውክልና ይሰጣል፤

IV. የካፒታል ዕቃ ምዝገባ የሚታገድበት ወይም የሚሠረዝበት ሁኔታ ሲያጋጥም በማስረጃ በማጣራትና በማረጋገጥ ምዝገባውን ያግዳል ወይም ይሠርዛል፤ እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃዎችንም ይወስዳል፤

V. ከካፒታል ዕቃዎች ምዝገባ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ህዝብ ሊያውቀው ይገባል ብሎ ያመነበትን መረጃ ይፋ ያደርጋል።

VI. ተከራይ ኢንተርፕራይዞች እዳቸው አጠቃለው ስለመክፈላቸው የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ክሊራንስ ከወሰዱ ቡኋላ የካፒታል እቃው የባለቤትነት መረጃ ይሰጣል

4.3 ባለድርሻ አካላት

አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ከካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅርቦት ጋር በተያያዘ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች እንዲቀረፉ የባለድርሻ አካላት ሚና አስፈላጊ በመሆኑ ይህንን ተልእኮ ለመወጣት የሚያስችል ተግባርና ሃላፊነት ተዘርዝረዋል፤

4.3.1 የገቢዎች ሚኒስቴር እና የክልል /የከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮዎች

I. በካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራ አዋጅ ቁጥር 103/1990 እና ተሻሻሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 807/2005 ዓ.ም መሠረት የካፒታል ዕቃዎች ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ ከታክስና ቀረጥ ነጻ እንዲገቡ ያደርጋል፤

II. ከቀረጥ ነጻ የገቡ የካፒታል ዕቃዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

III. ለኢንተርፕራይዞች ከአገር ውስጥ ከቫት ውጪ የሚቀርቡት የካፒታል ዕቃዎች የቫት ተመላሽ ገንዘብ በወቅቱ እንዲፈጸም ያደርጋል፤

IV. የካፒታል ዕቃ ተጠቃሚ በመሆን ወደ ሥራ የሚገቡ እና ሥራዎቻቸውን የሚያስፋፉ አንቀሳቃሾች ምርት አምርተው ወደ ገበያ በሚገቡበት ወቅት ግብር መክፈል እንዳለባቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ይሰጣል፡፡

4.3.2 የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተጠቃሚዎች ኃላፊነት

I. ለካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋሙም ሆነ ለሌላ ከሥራው ጋር ተያያዥነት ላለው አካል ትክክለኛ መረጃ ይሰጣሉ፤

II. በካፒታል ዕቃ ፋይናንስ የቀረቡላቸው የማምረቻ መሳሪያዎች በአግባቡ በመያዝ የመጠቀም፣ የመንከባከብ እና የመጠገን ኃላፊነት አለበቸው፤

III. በዋስትና ጊዜ በፋብሪካው ችግር ከማምረቻ መሳሪያዎች አጠቃቀም እና ብልሽት ጋር ተያይዞ ያጋጠማቸውን ችግሮች እንዲፈቱላቸው በወቅቱ ለአከራይ ያሳውቃል፤ በአቅራቢ ከተሰጠው የዋስትና ጊዜ ውጪ የሚኖሩ ጥገናዎች ራሱ በመሸፈን የማሽኑን ደህንነት ይጠብቃል፤

IV. የተረከቡትን የካፒታል ዕቃ መሸጥ፣ ማከራየት፣ መለወጥ፣ የማሽኑ አካል መቀየር፣ ሞዴፊክ መስራት፣ ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ እና ለአከራይ ሳያሳውቅ ከተተከለበት ወደ ሌላ ቦታ ማዛወር አይችልም፡

V. የኢንሹራንስ፣ የካፒታል ዕቃ እና የውል ምዝገባ ክፍያዎች የመሸፈን እና ሌሎች በውል የሚጠበቅባቸውን ግዴታዎች ይወጣሉ፤

5. በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ከባለድርሻ ተቋማት ጋር ተያይዞ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

5.1. የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት

- በዋጋና በጥራት ተወዳዳሪ የሆኑ የካፒታል ዕቃ አምራች/አቅራቢዎች በሚፈለገው ልክ የሌሉ መሆናቸው፤
- የኢንተርፕራይዞች ፍላጎት በሚፈለገው ልክ ለማስተናገድ የፋይናነስ ዕጥረት እያጋጠማቸው መሆኑ፤

- ከአለም ባንክ የሚደረገው የፋይናነስ ድጋፍ በኢትዮጵያ ልማት ባንክ በኩል ከሚሆን ለካፒታል ዕቃ ሊዝ ፋይናንስ ተቋማቱ በቀጥታ ፋይናንስ ቢደረግ፤
- በውል የተረከቧቸው ማሽኖች ከተተከሉበት ቦታ ያለ አከራይ እውቅና ማዘዋወር
- በኢንተርፕራይዞች ከአገር ውጪ የሚጠየቁ ማሽኖች በወቅቱ ለማቅረብ መቸገር
- በአገር ውስጥ የሚመረቱ የማምረቻ ማሽኖች በስታንዳርድ እና ጥራት ችግር ምክንያት ኢንተርፕራዞች የውጭ አገር ማሽኖች መፈለግ፤

5.2. ከተገልጋዮች አንጻር

- የካፒታል ዕቃ ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች የጥሬ ዕቃ አቅርቦት እጥረት፤
- የሚጠይቋቸው የካፒታል ዕቃዎች ፍላጎት ያለ ቢሆንም የእውቀት እና የክህሎት ክፍተት ያለ መሆኑ፤
- ኢንተርፕራይዞች በአገር ውስጥ የሚመረቱ የማምረቻ ማሽኖች የመጠቀም ፍላጎት ያለመኖር፤
- ኢንተርፕራይዞች በገቡት ውል መሰረት ክፍያ በወቅቱ ያለመፈጸም
- የማሽን አጠቃቀምና አያያዝ ችግር

5.3. ከማሽን አቅራቢዎች፣

- አቅራቢዎች እንደሚገልጹት ከውጪ የሚገዙ የካፒታል ዕቃዎች በውጪ ምንዛሬ ዕጥረት ምክንያት ማሽን በውል መሰረት በጊዜ ያለማቅረብ
- በአገር ውስጥ የሚመረቱ የማምረቻ ማሽኖች ኢንተርፕራይዞች በሚፈልጉት በጥራት፣ በዋጋ እና በብዛት የማምረት ተወዳዳሪ አለመሆን፤
- በኢንተርፕራይዝ የሚፈለጉት የማምረቻ ማሽኖች ለማምረት የስራ ማስኬጃ ፋይናንስ ዕጥረት አለባቸው፤
- ተወዳዳሪ እና በቂ የሆኑ የአገር ውስጥ አምራቾች እና አቅራቢዎች ያለመኖር፤

5.4. ባለድርሻ አካላት

- የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የማምረት ስራ ተግዳሮቶች ለመቅረፍ የድጋፍ እና ክትትል ውሱንነት
- ባለድርሻ አካላት አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በአገር ኢኮኖሚ ላይ ትልቅ ሚና እንዳላቸው ያለመገንዘብ፤
- የማምረቻ ቦታዎች፣ የመሸጫ እና የመሰረተ ልማት አቅርቦት ተግዳሮት
- የሥራ ማስኬጃ ብድርና የገበያ ችግር

- ለሊዝ ፋይናንስ ተጠቃሚዎች በአለም ባንክ በኩል ለስራ ማስኬጃ ተብሎ የሚሰራጨው የገንዘብ ድጋፍ አገልግሎት ለማግኘት በባንኮች በኩል ግልጽ የሆነ ግንዛቤ ያለመኖር፤
- መንግስት ለኢንተርፕራይዞች የሰጠውን የአገር ውስጥ የማሽን ግዢ የቫት ማበረታቻ ከሊዝ ኩባንያዎች የሚሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ለኢንተርፕራይዞች ያለመመለስ፤
- የቴክኒክ ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ለአምራቾች አስፈላጊውን ቴክኒካል ድጋፍ ያለመስጠትና ያለመደገፍ እንዲሁም በኢንተርፕራይዞች እንዲቀርቡ የሚጠየቁት የሚጠየቁት በቴክኖሎጂ ከፍ ያሉት የካፒታል ዕቃዎች የሚሰጥ ስልጠና ያለመኖር፣

6. የማጣቀሻ ጽሁፎች

- *የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት የሊዝ ፋይናንስ መመሪያ፣ 2014 ዓ/ም*
- *የካፒታል ዕቃ ንግድ ስራ አዋጅ ቁጥር 103/1990 እና የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 807/2005*
- *"Revised Lease Financeng Policy No. LFP/002/2022" የኢትዮጵያ ልማት ባንክ*
- *የካፒታል ዕቃ ፋይናስ ንግድ አ/ማህበራት የተለያዩ መመሪያዎች*
- *Limit on Capital goods Finance Exposure to a single lessee Directive No, CGFB/09/2019 (3rd Replacment, National Bank of Ethiopia*

....

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት

7. አባሪዎች

7.1. የካፒታል ዕቃ አቅርቦት ሂደት



7.2 የንግድ ዕቅድ ማቅረቢያ ቅጽ ናሙና

የንግድ ሥራ ዕቅድና የካፒታል ዕቃ ኪራይ መጠየቂያ ቅጽ

1. አመልካች መረጃ

አመልከች ህጋዋ ሰዉነትያለዉ ከሆነ የድርጅቱ የግል ስያሜ__________________________________

የኢንተርፕራይዙ ሥ/አስኪያጅ/ተወካይ ስም ከነአያት__________________________________

የአመልካችየተፈጥሮ ሰዉ ከሆነ ሙሉ ስም__________________________________

ጾታ____እድሜ_አመላካች የጋብቻሁኔታ__________________________________

2. አድራሻ

2.1 የፕሮጅክቱ የሥራአድራሻ፡-ክ/ከተማ ወረዳ___የቦታው ልዩ ስም/ሳይት____________________

መስሪያቦታው፡-የግል ☐ የመንግስትየመስሪያ ☐ ቦው የሼድ ወይም የቤትቁ_________የቦታው ስፋት በካ.ሜ._________ስ.ቁጥር መደበኛ _________________________________ሞባይል________

2.1 የመኖሪያ አድራሻ፡-ክ/ከተማ_____ወረዳ______የቤ.ቁጥር ________________________ስ/ቁ___________

3. የንግድ ሥራው መረጃ፡-

3.1.1 የኢንተርፕራይዙ አደረጃጀትና ህጋዊነት

3.1.1አደረጃጀት፡-

የግል(Propritorship) ☐ የሽርክና ማህበርPartnership) ☐ የህ/ስራ ማህበር(corporative) ☐

ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር (private Limited Company) ☐

3.1.2የተመሰረተበት ቀንና ዓ/ም_______የዕድገት ደረጃ_________መካከለኛ ከሆነየሽግግር ዙር___________

______________________የተሰማራበት የስራ ዘርፍ የስራ መስክ________________________

3.1.3.የንግድ ፈቃድ ቁጥር____

3.1.4.የግብርከፋይነትቁጥር____

3.1.5የኢንቨስትመንትቁጥር____

3.1.6 የተቋሙ የስራ መዋቅር አለ ☐ የለም☐ /ካለ ተያይዞ ይቅረብ/

3.1.7የሽያጭና ግዢ መመዝገቢያ መዝገብ አለ ☐ የለም ☐

3.1.7 የዕለት ገቢናወጪ መመዝገቢያ አለ ☐ የለም ☐

4. አደረጃጀት፣አስተዳደርና የሰው ሀይል

4..1የትምህርት ደረጃ እና የአባላት ብዛት

4.1.1ኢንተርፕራይዙ አባላት ብዛት ወንድ______ሴት__________ድምር _______

4.1.2የኢንተርፕራይዙ አባላት የትምህርት ደረጃ

4.1.2.1 ዲግሪና በላይ ብዛት__________________

4.1.2.2 ዲፕሎማና /ቴ/ሙያ ብዛት_____________

4.1.2.3.9ኛ-12ኛ ብዛት ______________

4.1.2.4.ሌሎች______________________

4.2.በሙያው ስልጠና የወሰዱ የኢንተርፕራይዙ አባላት ብዛት_________/ማስረጃ ይያያዝ/

4.3ከኢንተርፕራይዙ አባላት ውስጥ የአካልጉዳተኞች ወ--------- ሴ_________________ድ___________

4.4ከአባላቱ ውጪ የሆኑ የቅጥርሰራተኞች ብዛትወ--------- ሴ______________________ድ___________

4.5 የስራ ልምድ ____

5 የካፒታል ዕቃ ብድር ታሪክ መረጃ

5.1ኢንተርፕራይዙ ከዚህ ቀደም የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አገልግሎት አግኝቷል አላገኘም አግንቻለሁ☐ አላገኘሁም

5.2የአገልግሎቱ ተጠቃሚከሆነ፡- የማሽኑ ዓይነት_____________፣ _________________አገልግሎት የሰጠው ተቋም ስም _______________

ኪራዩ ተከፍሎ ተጠናቋል ☐ አልተጠናቀቀም ☐

6 ኢንተርፕራይዘ አሁን ያቀረበው የቋሚ ዕቃ ጥያቄ ዓይነት

የዱቤግዢኪራይ ☐ የፋይናንሻል ሊዝ☐

7.አገልግሎት የተጠየቀለት ሥራ

አዲስ ስራ ለመጀመር ☐ ነባርሥራ ለማስፋት ☐

8.ነባር ስራን ለማስፋትከሆነ

8.1.የኢንተርፕራይዙ ሲመሰረት የነበረው መነሻ ካፒታል_________________

8.2 በሚስፋፋው ስራ ወይም በአዲሱ ፕሮጀክት ሊፈጠር የሚችለው የስራ ዕድል ቋሚ______ ጊዜያዊ____

8.3 የተጀመረ የሶስተኛ ወገን የሥራ ውል (የገበያ ትስስር) ሥምምነት አ☐ ☐ የለም

ካለ የስራው ዓይነት፣ የገበያ ትስስሩ የፈጠረው ተቋም/መ/ቤት፣ ውሉ የሚያበቃበት ጊዜና በገበያ ትስስሩ የሚገኘው ገንዘብ መጠን ለማወቅ ማስረጃ ካለ የስራው ኮፒ ተያይዞ ይቅረብ፡፡

8.4.ኢንተርፕራዙ በሊዝ የጠየቃቸው ማሽነሪዎች ለንግድ ሥራው ምን ያህል ጠቀሜታ ይሰጣሉ ብለው ያምናሉ?____

____

9 የኢንተርፕራይዙ የብድር ታሪክ (መረጃ)

9.1ኢንተርፕራይዙ ከዚህ ቀደም የወሰደው ብድር ካለ

9.2.1 የአበዳሪው ተቋማት ስም ____

9.1.2የተበደረው የገንዘብ መጠን ድምር __________________

9.1.3ብድሩ ተመልሷል ☐

9.1.4በመመለስ ላይ ☐

9.1.5አልተበደረም ☐

- ከቁ. 9.1.1 — 9.1.5ያለው ማስረጃ ከአበዳሪ ተቋማት ተያይዞ ይቅረብ።

9.2.ኢንተርፕራይዙ አሁን ያቀረበው ወይም የሚያቀርበው የስራማስኬጃ ብድር ጥያቄ ካለ

9.2.1. የብድርመጠንበብር__________________

9.2.2. አገልግሎቱን የተጠየቀው የፋይናንስ ተቋም ስም______________

.9.2.3. 5የብድር ጥያቄው ያለበት ደረጃ፡- ጥያቄ አልቀረበም ☐ ጥያቄው ቀርቧል ☐

	15.1	13 የሂሳብሠንጠረዥ				
		Balance Sheet				
		AS AT: -----------------------------				
No	ሐብት (Asset)		ብዛት	የአንዱ ዋጋ	እጠቃላይየዋጋው ግምት በብር	መግለጫ
1	ጥሬገንዘብ (Cash):	A) በባንክያለ (In Bank)				
		B) በእጅያለ (On Hand)				
2	ወደፊትየሚሰበሰብ (Receivables)	A) ከዕቃሽያጭ (Accounts)				
		B) ከተስፋሠነዶች (Notes)				
3	በሱቅወይምበመጋዘንያለየሸቀጥመጠን (Goods In Stock)					
4	ለዕቃየተደረገየቅድሚያክፍያ (Prepayment On Merchandise)					
5	ተንቀሳቃሽሐብት (Current Assets)					
6	የፋብሪካዕቃዎችናመሣሪያዎች (Equipment And Machinery)					
7	ተሽከርካሪ (Motor Vehicles)					
8	የቤትናየቢሮዕቃዎች (Furniture And Fittings)					
9	ቤቶች (Building And Residencial House)					
10	ሌላተጨማሪሐብት (Other Assets)					
11	ቋሚሐብትየተጣራ (Fixed Assets (Net))					
12	ጠቅላላሐብት (Total Assets Birr)					
	ዕዳ (Liabilities)					
13	የሚከፈልዕዳ (Payable)	A) ለዕቃግዥ (Accounts)				
		B) የተስፋሠነዶች (Notes)				
14	ለግብርየሚከፈል (Tax Payable)					
15	የባንክብድር (Bank Loans)					
16	በረዥምዕዳዎችበዚህዓመትየሚከፈል (Current Portion, Long Term Debts)					
17	ሌላዕዳ (Others)					
18	በቅርብየሚከፈልዕዳ /ጊዜያዊዕዳ/ (Current Liability)					
19	በረዥምጊዜየሚከፈሉዕዳዎች (Long Term Debts)					
20	ካፒታልናመጠባበቂያዎች (Capital And Reserves)					
21	የዕዳናካፒታልድምር (Total Liability And Capital Birr)					

10 ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፋይፋ

10.1 ድርጅቱ ምን ያህል የስራ ዕድል ፈጥሯል___________ 10.2 ምን ያህል ለመፍጠር አቅዷል_

10.2የውጭ ምንዛሬ ለለማዳን ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ለመተካት ያለው አስታውጽዎ___

11.ምርትና የምርት ሂደት

11.1 የድርጅቱ ዎና ምርቱ ምንድን ነዉ?

11.2 ጥሬቃ ከየት ያገኛል?

12 የገበያትንተና

12.1 አስተማማኝገባያአለወይተፎካካሪዎችንማሽነፍምንምቹሁኔታአለ___________________

12.2 ዒላማ ገበያ(Target Market) ፕሮጀክቱ ምርቱን አገልግሎቱን ሊሸጥበት ስላቀደዉ ገበያና የሸማቹ ሁኔታ ይገለፅ________________________________

12.3አቅርቦትና ፍሰት ዳሰሳ የታቀደዉ ምርት/አገልግሎት ለማምረት የሚያስፈልገዉ ግብዓት በገበያ ውስጥ ያለው___

አቅርቦትና ገበያው ለምርቱ ያለዉ ፍላጎት ካለዉ የኢኮኖሚ ሁኔታ ጋር በማሳየት ይገለፅ___

13.4 ድርጅቱ በተመለከተ Swot Analysis

13.4.1ጥንካሬ

1. ___________________________
2. ___________________________
3. ___________________________

13.4.2 ድክመት

1. ___________________________
2. ___________________________
3. ___________________________

13.4.3 ምቹ ሁኔታ

1. ___________________________
2. ___________________________
3. ___________________________

14.የገበያ ስልቶች

14.1. ምን ያህል ያመርታል?___________________________________

14.2.ምርቱ የትና እንዴት ይሸጣል?_____________________________________

14.3.በምን ያህል ዎጋ ይሸጣል?_________________________________

14.4.የዋጋ ትመና ድርጅቱ የምርቱ/የአገልግሎቱ ዋጋ እንዴት ተመነ?_____

14.5.ከተፎካካሪ በተሻለ ደንበኞችን እንዴት መሳብ እንደሚቻል እንደታሰበ ይገለፅ_

14.6 የፕሮጀክቱ ምርት/አገልግሎት ከተወዳዳሪዎች ልዩና ተመራጭ የሚያደርጉ ሁኔታዎች ይገለፁ_

15. ፋይናንሽያል እቅድ

	15.2 Income statement					
15.2.1 .	**ገቢ (Income)ማሸኖች ከቀረቡ በኃላ የሚሸጡ ምርቶችን ጨምሮ**	መስኪያ	በወር የሚሸጠው ብዛት	የመሸጫ ዋጋ		መግለጫ
				ያንዱዋጋ	ጠቅላላ ዋጋ ብር	
1	ሽያጭ (Sales)					
2	የተሸጠዉ ዕቃ ዋጋ (Cost Of Goods Sold)					
3	መነሻ ዋጋዎች (Beginning Inventory As At Birr)					
4	ሲደመር የተገዙዕቃዎች (Add Purchases For The Period)					
5	ሲቀነስ መጨረሻ የቀሩ ዕቃዎች (Less Inventory As At)					
6	ሌሎች (Others)					
7	ያልተጣራ ትርፍ (Gross Profit)					
		መስኪያ	ብዛት	የወር ወጪ ግምት በብር	መግለጫ	
15.2.2	**ወጪዎች (Expense) ማሽኖች ከቀረቡ በኃላ የሚወጣ ወጪን ጨምሮ**					
1	ጥሬ እቃ					
2	ደሞዝ (Wages and Salary)					
3	የንግድቤትኪራይ (Business Premise Rent)					
4	ስልክ ማብራትናዉሃ (Utilities)					
5	ማደሻና ጥገና (Maintenance and Repair)					
6	መድን (Insurance)					
7	አገልግሎት ተቀናሽ (Depreciation)					
8	ሌሎች (Others Transport, Commission, Pension Expenses)					
	ጠቅላላወጪዎች (Total Expense)					
9	ትርፍከግብርበፊት (Income Before Tax)					
10	ግብር (Taxes)					
11	የተጣራትርፍከግብርበኋላ (Income After Tax)					
12	በዋስትናያለበትዕዳ (Guarantee Liability In Total)					

15.2.3 ሌሎችየኢንተርፕራይዙ /ተጓዳኝ/ የገቢምንጮችካሉ፡-

ተ.ቁጥር	የገቢውዓይነት	መለኪያ	ብዛት	የመሸጫዋጋ		የወሩ ተጨማሪ ገቢ ድምር በብር	መግለጫ
				ያንዱዋጋ	ጠቅላላ ዋጋ		
1							
2							
3							
4							
	ድምር						

16 .በፋይናንሻል ሊዚንግ ወይም በዱቤ ግዥ የተጠየቁት የካፒታል ዕቃዎች ዝርዝር

ተ.ቁ	የሚገዛው ካፒታል ዕቃ አይነት	ብዛት	የሚሰጠው አገልግሎት	የማሽኖቹ ስፔሲፊኬሽን (Specification)	ስሪት (አገር)	አቅራቢድርጅት	ገበያላይያለውየዋጋግምትበብር		መግለጫ
							የአንዱዋጋብር	ጠቅላላዋጋብር	
ድምር									

17. ወደ ኩባንያችን ከመምጣትዎ በፊት መረጃው ከየት አገኙ? (✓ ምልክት ይደረግ)

-- ከስልጠና/ዎርክሾፕ_____ -- ከሚድያ_______

-- ከቢልቦርድ/ዎል ብራንዲንግ__ -- ከንግድ ትርዒት/ባዛር_______ ከሌላ_______

18. የተሞሉት መረጃዎች ኢንተርፕራይዙን የሚመለከቱና ትክክለኛ መሆናቸውን፣ ለሚተላለፍልን የማምረቻ መሳሪያ የሚሆን የመሰረተ ልማት መሟላቱን፣ የጥበቃ ዋስትና፣ የመድህን ሽፋንና ከዋራንቲ በኃላ የጥገና ወጪዎች በራሳችን የምንሸፍን መሆኑን በፊርማችን እናረጋግጣለን፡፡

የብድር ጠያቂ ኢንተርፕራይዝ ስ/አስኪያጅ/ተወካይ ስም------------------------------

ፊርማ------------------------------

ቀን-------------------------------

<u>የኢንተርፕራይዙ አባላት</u>

ስ ም	ፊርማ

1. ____
2. ____
3. ____
4. ____
5. ____